# በኢትዮጵያ አገር አቀፍ የተዋሃደ ፓርቲ ጥያቄ ለምን?

ወይን የህወሓት የንድፈ ሃሳብ መፅሄት

መጋቢት 2011 ዓ.ም

መቐለ

ይዘት ገፅ


ከትንሳኤ ወደ ገሃነም ____ 3

በኢትዮጵያ አገር አቀፍ የተዋሃደ ፓርቲ ጥያቄ ለምን?____ 5

የፓርቲ ምንነት፣ አሰላለፍና ተልእኮ አጠቃላይ መነሻ ሃሣቦች____ 5

በኢትዮጵያ አገር አቀፍ የተዋሃደ አንድ ፓርቲ ምስረታ ጥያቄ ____ 22

ኢህአዴግን በአቋራጭ አንድ ፓርቲ ለማድረግ የሚፈልገው ኃይል ዓላማና ህልም____ 34

በፓርቲ ውህደት ጉዳይ ላይ የህወሓት ቱባ አቋምና ዋንኛ የመታገያ አቅጣጫዎች____ 41

**የአዘጋጁ መልዕክት**

**ከትንሳኤ ወደ ገሃነም...**

**"ታሪክ ራሱን እየደገመ ነው!"**

1983 ዓ/ም፤ ከግንቦት ሃያ በፊት፤ መላው የአገሪቱ ህዝቦች የሀገሪቱን ሁኔታ "ምድራዊ ገሃነም"ብለው የሰየሙት በታሪካችን እጅግ አስከፊው ወቅት እንደነበረ ይታወሳል፡፡ እስከ ፋሽሽታዊው የደርግ ስርዓት በነበረው የታሪክ ምዕራፍ የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰላም ናፍቋቸው፣ ዲሞክራሲ ተረግጦ፤ፍትሕ በአፍ ጢሙ ተደፍቶ፣ ልማት ለስሙ እንኳን የማይታይበት ሆኖ የጦርነትና የጭፍጨፋ ዘመናት እንዲገፉ ተገደዋል፡፡ ባጭሩ ይህች አገር እጅግ የተዳከመች፣ በውስጧ በነበረው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ምክንያት ለመበታተን ተቃርባ የነበረች፤ በዚህ ጦስ ሳቢያም ህዝቧ እርስ በራሱ ሊጨራረስ ጫፍ ላይ ደርሶ የነበረበት ወቅት ሲሆን፤ ባንፃሩ ሁኔታው እንዴት መፈታት እንዳለበት ማንም ሰው እርግጠኛ ያልሆነበት እጅግ ዘግናኝ አደጋ አንዣቦ እንደነበር ከቶ የሚረሳ አይደለም፡፡

ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይና ኢህአዴግ ባካሄዱት መራራ የትጥቅ ትግል ያበሰሩት የግንቦት ሃያ ድል የጥፋቱ ሁሉ ምክንያት የነበረውን ፋሽሽታዊውን የደርግ ስርዓት ከመደምሰስ ባሻገር በወቅቱ ሊፈጠር የነበረውን አደገኛ ሁኔታ በመቀልበስ ለዚህች አገርና ህዝቦቿ አዲስ መንገድ በመክፈት ትንሳኤዋን ያበሰረ ሆኗል፡፡ ከደርግ ውድቀት ማግስት በኋላ በነበሩት ጥቂት የሽሽግር ዓመታት የመበታተን ሳይሆን የመሰባሰብና የአንድነት ፈውስ የሰጠ፤ ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት የሚያስችል የማዕዘን ድንጋይ የተቀመጠበት፤ አንዣቦ የነበረው ከባድ አደጋ እንደ ጉም በኖ የመጪው ዘመን ተስፋ ጮራ የፈነጠቀበት ወቅት ነበር፡፡ ያ በኢህአዴግ የተፈጠረው የብሩህ ተስፋ ጮራ በየወቅቱ በሃቀኛ መስመርና ፕሮግራም ተመስርቶ በሚካሄደው የተግባር እንቅስቃሴ እየደመቀና እየሰፋ ባለፉት 27 ዓመታት ተአምራዊ ድሎች ሊመዘገብ ችሏል፡፡ በነዚህ ዓመታት በዋንኛነት ከሚጠቀሱት ክንዋኔዎች ውስጥ የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የቃል-ኪዳን ሰነድ የሆነው ሕገ-መንግስት ፀድቋል፤ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ተተክሏል፡፡ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ግብርና የሚመራው የልማት ስትራቴጂ ተነድፎ በምግብ ራስን በመቻልና ለገበያ የሚሆን ትርፍ ምርት በመላክ ረገድ ብዙ ርቀት ለመጓዝ ተችሏል፡፡ አገራችን በነፃ የገበያ ፖሊሲ የምትመራ አገር ሆናለች፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ተደማምረው የአገራችን ህዝቦች መሰረታዊ ጥያቄዎች የሆኑት ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማትን በአስተማማኝ ሁኔታ ምላሽ የሚያገኙበት ዕድል መፍጠራቸውንና በየግዜው እየጎለበቱ እየሄዱ እንደነበረም የሚታወቅ ሃቅ ነው፡፡

"ታሪክ ራሱን ይደግማል" እንደሚባለው ሆነና በኢትዮጵያ በአንድ ወቅት የነበረው የዕድገት ከፍታ ጠርዝ በረጅም ግዜ የቁልቁለት ጉዞ ተተክቶ ከቆየ በኋላ ዳግም ተመልሶ በህዝቦች መራራ ትግልና በበሳል አመራር ወደ ነበረበት ከፍታ መውጣት ጀምሮ የነበረው የትንሳኤና የህዳሴ መዋእል ተገትቶ፤ ዳግም ወደ ተሻገርነው

አሳፋሪ የአዙሪት መንገድ እየተመለስን እንገኛለን፡፡ በከፈልነው ከባድ መስዋእትነት የኢትዮጵያ ህዝቦችን ሁሉ ከዘመናት ጭለማና የማሽቆልቆል ጉዞ ወደ ብርሃንና ትንሳኤ ያሸጋገረውና የህዳሴ ተስፋ ጮራ ያመላከተው ህወሓት/ኢህአዴግ የታገለለትንና የድሎቹ ምንጭ የሆኑት ፕሮግራሙ፣ ራእዩና መስመሮቹ ታግተው አገርና ህዝብ በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ኢህአዴግ ከመፈጠሩ በፊት ወደ ነበረው የገሃነም ዘመን እያመሩ ይገኛሉ፡፡

ኢትዮጵያና ህዝቦቿ በመራራ ትግላቸውና መስዋእትነታቸው ያረጋገጡት ህገ መንግስታዊ ስርዓት በኢህአዴግ ድርጅት ውስጥ ባቆጠቆጡ ጥገኞች ማን አለብኝነት መፈራረስ መጀመሩ የሚታይና ተጨባጭ ሃቅ ነው፡፡ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ መስመር የሚመነጩ የድርጅቱ ፅኑ እምነቶችና መመሪያዎች በጠራራ ፀሐይ ተቀምተው በጥገኛው የመበስበስ ኃይል አስተሳሰብና ፕሮግራም እየተተኩ ይገኛሉ፡፡ ባጭሩ ኢህአዴግ ቀብር ብቻ ይቀረዋል ካልተባለ በስተቀር የሞተ ድርጅት ሆኗል ቢባል ነባራዊ ሁኔታው ይገልፀዋል፡፡ በዚህ መንገድ የሚገለፀው የበከተ ድርጅት ደግሞ ይቅርና ጠንካራና ተአምራዊ ለውጥ ያስመዘገበውን ኢህአዴግ ፈለግ ሊከተል አገርና ህዝብን ለመምራት የሚያስችለው ዓቅምና አንድነት አይኖረውም፡፡ ኢህአዴግ በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ሂወት አልባና ባዶ ቀፎ ሆኖ የሚታይ ሲሆን ኢትዮጵያንና ህዝቧን አይመራም ብቻ ሳይሆን መላ አገሪቱን ከ27 ዓመት በፊት ወደ ነበረው የጥፋት ዘመን ይዟት እየጠፋ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በየቀኑ የሚነገሩ ያልተለመዱ ዜናዎችም የሚያረጋግጡትም ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

አሁን የኢህአዴግን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለከተው በጥገኛ መበስበስ አዘቅት ውስጥ እያዳከረ የሚገኝ ሲሆን የሚወስዳቸው የቀቢፀ ተስፋ እርምጃዎች ደግሞ ሞቱንና ቀብሩን በማፋጠን ላይ ናቸው፡፡ ኢህአዴግ አሁን ባለበት የመከነ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ “አገር አቀፍ የፓርቲ ውህደት” ለመተግበር መፍጨርጨር መጀመሩ ከንድፍ ሃሳቡ፣ ከመርሆዎቹና ከመስመሩ ጨርሶ መውጣቱን ያመላክታል፡፡ ኢህአዴግን በአቋራጭ አንድ ፓርቲ ለማድረግ የሚፈልገው ሀይል ዓላማውና ህልሙ ኢህአዴግን ማጠናከር ሳይሆን ጨርሶ በማፍረስ ግበአተ መሬቱን በመፈፀም አብዮታዊ ዲሞክራሲና መሪ ድርጅቱን የማጥፋት ተልእኮ ያነገበ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እየሰመረለት ያለ ይመስላል፡፡ በህወሓት የምትዘጋጀው ወይን የንድፈ ሃሳብ መፅሔትም ይህን ዓብይ ጉዳይ ያማከለ የኢህአዴግ ወቅታዊ ሁኔታ በአገራዊ ሁኔታ ውስጥ ያለበትን ቦታ፣ ጉዳይና በተለያዩ አቅጣጫዎች እየተነሳ በሚገኘው የአንድ ፓርቲ ውህደት ጥያቄ ላይ የህወሓትን ግልፅ አቋም እንዲሁም በቀጣይ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ስራዎች በሚመለከት የቀረበውን ትንተና ለአባላቷ አዘጋጅታለች፤ መልካም ንባብ!

## ወቅታዊ ጉዳይ

# በኢትዮጵያ አገር አቀፍ የተዋሃደ ፓርቲ ጥያቄ ለምን?

## 1. መግቢያ

በአገራችን የተለየ ፖለቲካዊ ሁኔታ ከጀመረበት ግዜ አንስቶ ህወሓት በየግዜው የሚታዩ የሁኔታ ክስተቶችን እየተከታተለ በሳልና ትክክለኛ አቋም በመያዝ ቀና የትግል አቅጣጫዎችን እየነደፈ ሲታገል ቆይቷል፤ አሁንም በመታገል ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡ መልክ እየያዘ የመጣውን ሁኔታና አጠቃላይ ዕድገቱን እንደ አንድ ምዕራፍ በማጤን መሰረታዊ ግምገማና የትግል አቅጣጫዎችን አስቀምጠናል፡፡በየግዜው እየተከሰቱ ያሉ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በቅርበት እየተከታተልን ካስቀመጥነው አጠቃላይ የትግል አቅጣጫ ጋር እያገናዘብን ዕለታዊ ስራዎቻችንን መምራት እንዳለብንም ተግባብተናል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ አዳዲስ ክስተቶችና ተጨማሪ ውይይቶች ማካሄድና አቋሞችን መውሰድ የሚፈልጉ ጉዳዮች ሲኖሩ ደግሞ በየግዜው እያበሰልናቸው መሄድ የግድ እንደሆነም አስቀምጠናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል በአንዱ ወይም በሌላ መንገድ ሲነሱ የነበሩ ሦስት ወይም አራት አንገብጋቢ ጉዳዮች በአገሪቱ ወቅት ከጊዜ አኳያ እየቀረቡ እንደ ጉዳይም ትልቅ ቦታ እየያዙ እየመጡ ናቸው፡፡ እነዚህም የአንድ ፓርቲ ጥያቄ፣ የ2012 ዓ/ም ምርጫ፣ የማንነትና የወሰን ኮሚሽን አፈፃፀም እንደዚሁም ብሄርተኝነት (ዴሞክራሲያዊ፣ ፅንፈኛ፣ የዜግነት ወይም ሲቪክ ናሽናሊዝም) የመሳሰሉት ዓበይት ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸው ጉዳዮች ሆነው በክልላዊና አገራዊ መድረኮች አጀንዳነታቸው ጎልቷል፡፡  በነዚህ ጉዳዮች ላይ ተጨባጭ ሃሳቦችን ይዘን ፅሑፍ ወይም ጥናት ቀርቦባቸው አቋም የወሰድንባቸውን ልናጎለብታቸው፣ በጥልቀት ያላየናቸውን ደግሞ ልናያቸውና ተከታታይ የውይይት አጀንዳዎች እንዲሆኑ ተይዘዋል፡፡ ለዛሬ አገር አቀፍ የፓርቲ ውህደት ጥያቄ በአገራችን ለምን? እና የ2012 ዓ/ም ምርጫ የሚመለከቱ መነሻ ፅሑፎች ቀርበዋል፡፡ የፓርቲ ውህደት ጥያቄን በተመለከተ በአገራዊ ሁኔታ ላይ አዲስ ትኩሳት የሚያስነሳ ቁልፍ ነጥብ ተደርጎ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ለመደገፍ አልያም ለመቃወም መነሻችን ምን ይሁን? ምን ዓይነት የትግልና የመመከት አካሄድ ይኑረን? የሚሉትን በውይይት የምናጎለብታቸው ሆኖ ለመነሻነት ያህል ይህ ፅሑፍ ቀርቧል፡፡

## የፓርቲ  ምንነት፣ አሰላለፍና ተልእኮ አጠቃላይ መነሻ ሃሣቦች

### 1.1 የፓርቲ  ምንነትና ዕድገት

i. የሰው ልጅ ታሪካዊ ጉዞ እንደሚያረጋግጠው ሰው ከመነሻው ማሕበራዊ እንስሳ ነው፡፡ የሰው ልጅ በየግሉ ተበታትኖ የሚኖርና ሊኖር የሚችል ሳይሆን ለመኖር ሲል ከአምሳያዎቹ ሰዎች ጋር መስራትና አብሮ መኖር የግድ የሆነበት ፍጡር ነው፡፡ እነዚህ ዝምድናዎችም የሰው ልጅ  ለመኖር የግድ

ሊያሟላቸው የሚገባ የምርት ሂደቶች የሚፈጥራቸው ስለሆነ ቢፈልግም ባይፈልግም የግድ መኖር ያለባቸው ዝምድናዎች ናቸው፡፡ ለመኖር በማምረት ላይ የተመሰረተ ዝምድና መፍጠር ወደ ማምረት መግባት አለበት፡፡ እንደዚህ ያለ የምርት ሂደትን በተናጠል መፈፀም ስለማይቻልና ሰፊና መሰረታዊ ትስስርና መደጋገፍ የሚጠይቅ ስለሆነ የሰው ልጅ ህልውናውን ለመጠበቅ ሲል የሚያካሂደው ምክንያታዊ የምርት ግንኙነት ተግባር የማይበጣጠስ ማህበራዊ ህይወት ማለትም ቤተሰባዊ፣ ጎሳዊ፣ ብሄረሰባዊ፣ ብሄራዊ፣ አገር አቀፋዊ ብሎም ዓለም አቀፋዊ ትስስሮች እየፈጠረ መጣ፡፡

ii. በዚህ ኢኮኖሚያዊና የምርት ሃይሎች ታሪካዊ ዝምድና ውስጥ ሰዎች ባደረጉት እንቅስቃሴና ጥረት ከእንስሳት ማደን፣ አትክልትና ፍራፍሬ ለቅሞ ከመኖር እየተላቀቁ ወደ እርሻ፣ የእንስሳት እርባታና እደ ጥበብ እየተሸጋገሩ በሄዱ ቁጥር ልዩነት እየተፈጠረ ሀብታምና ድሀ፣ ገዢና ተገዢ ወዳለበት ቦታ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት የኑሮ ዘይቤ እየተሸጋገረ መጣ፡፡ እንደዚህ ያሉ አዳዲስ የዝምድና ዕድገቶች በህብረተሰቡ ውስጥ እየተፈጠሩ በመምጣታቸው የመደቦች ክፍፍል ተጀምሮ እየጎለበተ መጥቷል፡፡ ከጋርዮሽ ስርአት ወደ ግል ባለቤትነት እየተሸጋገሩ የመጡ በመደቦች መካከል ግጭት እየተፈጠረ መደባዊ ትግል እየሰላ በሁሉም የትግል አግባቦች አንድ ስርዓት በሌላ ስርዓት እየተተካ አዳዲስ ገዢ መደቦችና አዳዲስ ጭቆና እየተፈጠሩ ህብረተሰባዊ ግንኙነት በእንደዚህ ዓይነት እንቅስቃሴ ወደፊት እየተራመደ መጥቷል፡፡

iii. በዚህ ዓይነት አሰራር እየጎለበተ የመጣው የፌደራላዊ ስርዓት ማህበረሰብ በካፒታሊስት ስርዓት መተካቱን ተከትሎ ከተፈጠረው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚና የውድድር ባህሪ ጋር ተያይዞ የፓርቲዎች መፈጠር፣ መጠናከርና መዳከም ሁኔታዎች እየተፈጠረ መጥቷል፡፡ በተለይም ከነፃ ኢኮኖሚ ገበያ ማበብ ጋር ተዛምዶ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመርያ የፖለቲካ ፓርቲ መፈጠር ይፋ እየሆነ መጥቷል፡፡ ቡርዥዋው መስፍናዊ ስርዓትን በማፈራረስ የነፃ ገበያ ግንባታ በሚያጧጡፍ ወቅት በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካውም በኩል ሃይለኛ ውድድር ይፋ እንዲሆን አደረገ፡፡ ይህ ውድድር መውጫ የሌለው ቀውስና የስርዓት መናጋት እንዳያስከትል ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር የሚያሰፍን የቡርዥዋ ዴሞክራሲ የግድ ብሏል፡፡ በራሱ በቡርዥዋው መካከልና ከተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በሚፈጠረው የጥቅም ውድድርና ግጭት ምክንያት ስርዓቱ አደጋ ላይ ሳይወድቅ በሰለጠነ፣ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ለመወያየትና ፍላጐታችን ለመገደብ የሚቻልበት አንፃራዊ ፖለቲካዊ መፍትሄ የዲሞክራሲና የፓርቲዎች ህልውና ሆነ፤ በዚ ዓይነት አሰራርና አፈጣጠር የፓርቲዎች ዕድገት አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡

## 1.2 የፓርቲ አሰላለፍ፣ ተልእኾና ማህበራዊ መሰረት

i. ፓርቲ ማለት የአንድን መደብ ተጨባጭ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሰለፍ ፓለቲካዊ ድርጅት ነው፡፡ አንድ መደብ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ጥቅሞቹን ለማረጋገጥ ፖለቲካዊ ስልጣን ለመጨበጥ የሚመራው የመደቡ ፖለቲካዊ ድርጅት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ ፖለቲካዊ አደረጃጀት ነው ፓርቲ የሚባለው፡፡ ይህንን እውነታ "መለያ እምነቶቻችን" የተሰኘው መፅሓፍ በገፅ አንድ ላይ እንዲህ ይገልፀዋል፤ "የፖለቲካ ድርጅቶች የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥቅም በመወከል ነው የሚቋቋሙት፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ፖለቲካዊ ድርጅት 'ለተወሰኑ ሃሳቦች እንጂ ለማንኛውም የህብረሰተብ ክፍል በመወገን የቆምኩ አይደለሁም' የሚለውም ጭምር ዞሮ ዞሮ የአን ን ወይም የሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም የሚወክል መሆኑ አይቀርም፡፡ ፖለቲካዊ ድርጅቶች የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ወኪል የሚሆኑት የህብረሰተሰብ ክፍሉን 'ወክየሃሎህ' ስላሉት ወይም 'አልወከልክሁም' ስላሉት ሳይሆን የያዟቸው ዓላማዎችና የነደፏቸው ፖሊሲዎች፣ የሚከተሏቸው አሰራሮች ወዘተ በመሰረታዊነታቸው የአንዱን ወይም የሌላውን ህብረተሰብ ክፍል ጥቅም የሚያስጠብቁ ስለሆኑ ነው" ይላል፡፡

ii. ፓርቲዎች መፈጠር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ በመሰረቱ ለአንድ መደብ ወይ ማህበራዊ ክፍል ተሰልፈው ወግነው የቆሙ ነበሩ፤ ለቡርዥዋው ወይም ለሰራተኛው ወይም ለአርሶ አደሩና አጋሮቹ፡፡ ሁሉም ፓርቲዎች በዋነኛነት የአንድን መደብ ጥቅምና ስነ ሃሳብ የሚያራምዱ መሰረታዊ ወገንተኝነታቸውንም ለዚሁ መደብ አድርገው ሌሎች ከመደቡ ጋ የጋራ ጥቅም ያላቸውን በአጋሪነት በመያዝና በማሰለፍ ጥቅሞችን የሚያስከብር ፖለቲካዊ ፕሮግራም፣ ስትራቴጂና ስልት እንደዚሁም አሰራሮችን ነድፈው የሚተውኑ ናቸው፡፡ በተለያየ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ባላቸው መደቦች መካከል የሚደረገው ትግል በመሃል ቦታ የሚቆም ወይም ደግሞ የሁለት ተፃራሪ መደቦችን ጥቅም በአንድ ላይ አስጠባቂ ሆኖ የሚገኝ ፓርቲ አይኖርም፡፡ከዚህ ይልቅ የአንዱን መደብ ጥቅም የሚያስጠብቅ የሌላውን መደብ ጥቅም ግን የሚፃረር ነው የሚሆነው፡፡

iii. እስካሁን በዓለም ላይ የተካሄዱ አብዮቶችና አሁንም ያሉ አሰላለፎች በይፋ የሚያሳዩት ይህንን ሃቅ ነው፡፡ከነፃ ገበያ መፈጠር ጋር ተያይዘው የቡርዥዋውና የሰራተኛው ስነ ሃሳቦች የተከሰቱ ሲሆን የመደቦቹን ጥቅም የሚወክሉ የዲሞክራሲና ፓርቲ ገፅታዎች እየተጠናከሩ መጥቷል፡፡ ሊበራል ዲሞክራሲ በኢንዳስትሪ በበለፀጉት አገሮች የላይኛው ቡርዥዋ ተወካይ ሆኖ በተለያዩ ስሞች የሚጠራ እንደ ሪፓብሊካንና ኮንሶርቫቲቭ በሌላ መልኩ ደግሞ በዚያው ስርአት ጥቅም ዙርያ ሶሺያል ዲሞክራሲ በሚል ሲጀምር ኮሚኒስት የነበረው አስተሳሰብም ቀስ በቀስ በነፃ ገበያ ጉያ ውስጥ በብርዥዋው ጥቅም ዙሪያ ሆነው መጠነኛ ጥገናዊ ለውጥ በማድረግ የሰራተኛውም ሆነ የሌላ ንኡስ ከበርቴ ችግርን በድጎማ ለመፍታት አልመው የሚነቀሳቀሱ ፓርቲዎች (እንደ ሶሺያል ዲሞክራት፣ ዴሞክራቲክ፣ ሌቨር ወዘተ ...የመሳሰሉት) ከዚያም አልፎ የሰራተኛውን መደብ ሙሉ በሙሉ የሚደግፉ

ኮሚኒስት ፓርቲዎች እንደዚሁም ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ በተለያዩ አገሮች ዓላማችን አርሶ አደሩን ማእከል በማድረግ ሌሎች ጭቁኖችንም በዙሪያው በማሰለፍ በነፃ ገበያ አጥር ውስጥ ሆኖ ለአርሶ አደሩና አጋሮቹ በመወገን ተጠቃሚ የሚያደርግ አብዮታዊ ዲሞክራሲና ለዚህ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ዓላማዎች የሚታገሉ ፓርቲዎች ደግሞ እየጎለበቱ መጥተዋል፡፡

iv. በአጠቃላይ በ19ኛውና በ20ኛው ክፍለ ዘመናት የተፈጠሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ማህበራዊ መሰረታቸው በዋነኝነት አንድ መሰረታዊ መደብ ነው፡፡ ይህም ማለት ፓርቲዎቹ በወገናዊነት የሚታገሉለት መደብ ቡርዥዋውን ወይም ሰራተኛውን አልያም አርሶ አደሩን ነው፡፡ይህም የመላው ህዝብ የሚባል ሳይሆን የዋናው ማህበራዊ መሰረትና አጋሮቹ ጥቅም ማረጋገጥ ነው፡፡ በሂደት ከነበራዊ ሁኔታዎች ለውጥ ጋር ተዛምዶ የሚመጣው የዓላማ፣ የፖሊሲና የአሰራር ለውጥ ወይም ማሻሻያ ዞሮ ዞሮ የወገኑለትን የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም በላቀ ደረጃ ለሟሟላት የሚያስችል ስለሆነ አሰላለፉን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ከድርጅት ድርጅት የሚያመሳስላቸውና የሚለያያቸውም አለ፡፡

v. በመሆኑም የፓርቲዎች ወገንተኝነት የሚለየው በመለያ ነጥቦች ባህሪያቸው ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት “መለያ እምነቶቻችን” የተሰኘው መፅሐፍ በገፅ አንድ ላይ በግልፅ እንዲህ ይላል፤

”የድርጅቶች ማንነትና አሰላለፍ የሚለየው ዓላማቸው፣ ፓሊሲዎቻቸውና አሰራራቸው ማንን ለመጥቀም ተብሎ እንደተነደፈ በተጨባጭም ማንን እንደሚጠቅም በማየት ነው የሚመለሰው ሲባል ፤ ድርጅቶች በሚከተሉት ዓላማና ፖሊሲዎች መካከል ምንም የሚያመሳስል ነገር አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ አንድን ድርጅት ማንነቱን የሚገልፀው፤ ድርጅቱን ከሌላው ድርጅት የተለየ የሚያደርገው ፤ ያንን ድርጅት ከሌላው የሚመሳስለው ነጥብ ሳይሆን ከሌላው የሚለየው ነጥብ ነው፡፡”

Vi. ይህንን መነሻ በማድረግ ነው የድርጅቶች መለያ ነጥብ ነጥሮ የሚወጣው፡፡ የድርጅቶቻችን መለያ ነጥቦች በማነፃፀር ብቻ ነው የድርጅቶች ሃቀኛ ማንነታቸውንና መሰረታዊ አወጋገናቸውን ለማወቅ የሚቻለው፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቃልና በመልክ ደረጃ የሚሉትንና የሚቀበሉትን የሚመሳሰለው ነገር ሁሉ ግዜ የሚታይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም በመሰረታዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳይ ላይ አንድ አይደሉም፡፡አንዳንዶቹ በአንድ አጥር ሆነው ጭቁኖቹ ሊያገኙት የሚችሉት የላቀ ጥቅም እንዲያገኙ ለይተው ይታገላሉ፤ ሌሎች ደሞ የዚህ ተፃራሪ የሆነ ዓላማ ይይዛሉ፡፡ ስለዚ በአጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ተመሳሳይ የሚመስል ነገር ቢኖራቸውም ማንነታቸውንና አሰላለፋቸውን የሚወስነው የዓላማ፣ የፖሊሲና አሰራር ልዩነት ላይ የሚመሰረት የውግንናና አሰላለፍ ልዩነት ባላቸው መለያ ነጥቦች ነው፡፡ አጠቃላይ መነሻ በነዚህ መነፅሮች በመንደርደር የኢህአዴግን ምስረታ፣ አሰላለፍ፣ ተልእኮና ማህበራዊ መሰረት ወደ ማየት እንሸጋገር፡፡

## II. የኢህአዴግ ምስረታ፣ አሰላለፍ፣ ተልእኮና ማህበራዊ መሰረት

### 2.1 አጠቃላይ መነሻ

#### 2.1.1 በማህበረሰብ ዕድገት የብሄሮችና አገሮች የምስረታ ሂደት በአጭሩ (ከህወሓት ጥናታዊ ፅሑፎች የተወሰደ )

i. በዚህ ፅሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ላይ ባጭሩ እንደተነሳው የሰው ልጅ ለመኖር ሲል ከአምሳያዎቹ ሰዎች ጋር የሚፈጥረው ግንኙነት ለሰው ልጅ ህልውና ሲባል ትስስሩና ልምዱ ቀጣይነት ያለው ይሆናል፡፡ ይህ ትስስር ሁሉንም አባላቱን የሚያቅፍ ቀጣይነት ያለው ማህበራዊ ቁርኝት ይሆናል፡፡ ሁሉም አባላቱ ደግሞ እንደ አንድ አካል ሆነው ማህበራዊ ተግባራቸውን ያካሂዳሉ፡፡ ማህበራዊ ትስስሩም እንደሁኔታው እየሰፋና እየጎለበተ ይሄዳል፡፡ የማምረቻ መሳሪያዎች ዕድገት ዝቅተኛ በሆነበት ህብረተሰባዊ ትስስሩም ጠባብ ይሆናል፡፡ የመገልገያ መሳሪያዎች እየጎለበተ በሚሄድበት ወቅት ደግሞ ሰፊ ህብረተሰባዊ ትስስር እያደገ፣ ጠባቡም በሰፊው ህብረተሰባዊ ትስስር እየተተካ ነው የህብረተሰብ እድገት የመጣው፡፡

ii. ከዚህ በመነሳት የመጀመሪያው የህብረተሰብ ትስስር በቤተሰባዊ ትስስር ነበር፡፡ (ይህ ያሁኑ የባልና ሚስት ትስስር አይደለም፤) ይህ ቤተሰባዊ ትስስር በአጠቃላይ አንድ የዘር ግንድ ያላቸው ሰዎች የሚሰባሰቡበት ነበር፡፡ ስለሆነም በየግዜው የመገልገያ መሳሪያዎች እየተሻሻሉ ሲሄዱ የሚፈፀሙት ማህበራዊ ተግባራት ብዙ የሰው ጉልበትና ሰፊ ትብብርን የሚጠይቁ እየሆኑ ሲመጡ ቤተሰባዊ ትስስር በሌላ ሰፋ ያለ ህብረተሰባዊ ትስስር ማለትም በነገዳዊ ማህበራዊ ስብስብ ተተካ፡፡ ይህ ትስስር የጋራ ትውልዳዊ ቁርኝት ያላቸውን ቤተሰቦች የሚያቅፍ ትስስር ነው፡፡ ይህም በሂደት በቀጠለው የመገልገያ መሳሪያዎች መሻሻል ሳቢያ መፈፀም ያለበትን ማህበራዊ ተግባር ለማስኬድ የቆየው ትስስር ብቃት የሌለው ሆኖ በመምጣቱ በሌላ ሰፋ ያለ መሰረት ያለው ጎሳዊ ወይም የዘር ትስስር ተተካ፡፡ ይህ ትስስር ከፍተኛው የጋርዮሽ ስርዓት ሕብረተሰብ ሆኖ ነገዶችን ያቀፈ የላቀ ጎሳዊ ማህበራዊ ቁርኝት በመሆን አባላቱን እንደ አንድ አካል አድርጎ ይቆጥር ነበር፡፡

iii. የህብረተሰብ ዕድገት እየቀጠለ ሲሄድ መደቦች መብቀል ጀመሩ፤ የባሪያ ህብረተሰብ መሰረት ሲባል አከባቢያዊ ትስስር አዲሱን ዕድገት የማይሸከምና የማይስማማ ሆኖ በሌላ ተተካ፡፡ ያ ማቆጥቆጥ የጀመረው ህብረተሰብ ግን አድሏዊና ሰዎች በሰዎች በንብረትነት የሚያዙበት ሂደት በመሆን እንደ ንብረት የሚቆጠሩ ባሪያዎችን በአመዛኙ ከሌሎች ጐሳዎች በማምጣት ቀጠለ፡፡ ይህም የህብረተሰብ ማህበራዊ ኃይል ከአንድ ዘር ያልበቀለ ህብረተሰባዊ ትስስር ፈጠረ፡፡ ከባሪያ ህብረተሰብ መፈጠር ጋር ደግሞ ተበዝባዥ ባሪያዎችን ጨቁኖ የሚያዝ የጭቆና መሳሪያ ማለትም መንግስት ተፈጠረ፡፡ የተለያዩ የዘር ግንድ ያላቸው ሰዎች በአንድ መንግስት ጥላ ስር በአንድ ድንበር ወይም ወሰን፣ የሚያግባባቸው የጋራ ቋንቋ፣ አመጣጣቸውን የዕድገታቸው ሂደት የሚገልፅ የጋራ ታሪክ፣ ስነ አእምሮአዊ

አስተሳባቸውን የሚገልፅ የጋራ ባህል በመፍጠር ብሄረሰባዊ ትስስር እየተባለ የሚጠራ ህብረተሰባዊ ትስስር ተተካ፡፡ ይህ በባሪያ ህብረተሰብ ተፈጥሮ በፊውዳሉ ህብረተሰብም የቀጠለ ማህበራዊ ስብስብ ነው፡፡

iv. በዚህ መልኩ የህብረተረሰቡ ዕድገት ቀጠለ፡፡ በባሪያና በመስፍናዊ ስርዓት የህብረተሰቡ ኢኮኖሚ ሰርቶ ወደ ገበያ አውጥቶ በመሸጥ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ለራስ በመጠቀም ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የምርት መገልገያ ጎልብቶ የሸቀጥ ምርት እየተስፋፋ፣ ንግድና መጓጓዣ እየተሻሻለ በተለያዩ አከባቢዎች የብሄረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንደ ጥቅል ኢኮኖሚያዊ ኑሮ በማጎልበት በመካከላቸው ያለው ትስስር፣ ግንኙነትና ትውውቅ ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር በድንበር፣ በጋራ በቋንቋ፣ በታሪክና በባህል እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ ኑሮ የሚመራ ብሄራዊ ትስስር በመፍጠር ማህበራዊ ስብስቡ በብሄር ሊተካ ችሏል፡፡ በመሆኑም ብሄሮች የአዲስ ጨቅላ ካፒታሊስት ብቻያ እየሆኑ መጡ፡፡ ካፒታሊዝም ሲፈጠር ብሄሮችም አብረው ተፈጠሩ፡፡ ካፒታሊዝም ወደ ላቀ ደረጃ ሲሸጋገርና የተደራጀ የብሄር ኢኮኖሚያዊ ሂወት ሲጎለብት ብሄራዊ ስብስቡ እየጠበበው በዓለም ደረጃ ሊኖር ወደ ሚችለው ማሕበራዊ ስብስብነት ተሸጋገረ፡፡

v. “መንግስት” የሚባለው ክስተት በባሪያው ስርዓት ሕብረተሰብ የተፈጠረ ቢሆንም እንኳን የጋራ አንድወጥ አገር ያለው መንግስት የሚፈጠረው ኣብዛኛውን ጊዜ ከካፒታሊዝም መብቀል ጋር ተያይዞ ነው፡፡የተደራጀ አገርና መንግስት ለመፍጠር የሚያስፈልገው ፈጣን የመጓጓዣና መገናኛ ከካፒታሊዝም መብቀል ጋር ስለሚመጣ ነው፡፡ ብሄሮች የሚበቅሉትም ከካፒታሊዝም መብቀል ጋር ነው፡፡ በመሆኑም ብሄሮች የበቀሉበትና የተደራጀ መንግስት መተከል የጀመረበት ወቅት በአመዛኙ በአንድ ወቅት ጎን ለጎን የተራመዱበት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ሂደት እያንዳንዱ ብሄር የገዛ ራሱን መንግስት መስርቷል ማለት ግን አይደለም፡፡ ካፒታሊዝም በስርዓት የጎለበተባቸውና ያልጎለበተባቸው አገሮች ወይም ብሄሮች ዕድላቸው ተለያይቷል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነንን የምዕራቡና የምስራቁ ዓለም ሂደት የበለጠ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

vi. የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊዝም በመደበኛው መንገድ የጎለበተ በመሆኑ የተደራጀ መንግስት የመመስረትና የተደራጀ ኢኮኖሚያዊ አኗኗር የነበራቸው ብሄሮች የመፍጠር ሂደት በአንድ ወቅት ጎን ለጎን ነበር የተካሄዱት፡፡ በውጤቱም አብዛኛዎቹ የበቀሉት ብሄሮች ራሳቸውን ችለው የተደራጀ መንግስት በመመስረት ብሄራዊ መንግስት ፈጥረዋል፡፡ በአብዛኛው ምስራቅ አውሮፓ፣ አፍሪካ፣ ኤስያና ላቲን አሜሪካ ካፒታሊስት ስርዓት በተለመደው የዕድገት አገባብ አልሄደም፡፡ ካፒታሊዝም በአግባቡ ሳይበቅል በተለያየ ምክንያት የተደራጀ መንግስት ተፈጠረ፡፡ አንድ የተደራጀ መንግስት በውስጡ የተለያዩ ብሄረሰቦችን ይዞ ተመስርቷል፡፡ ተደራጀው መንግስት ከተመሰረተ በኋላ ካፒታሊዝም እያደገ መጥቶ በሂደት ብሄረሰቦቹ ወደ ብሄር  አድገው የራሳቸው መንግስት ሳይመሰርቱ አስቀድመው በሌላ

ብሄር ስር ታስረው ስለቆዩ የመንግስት ስልጣንን የተቆጣጠረው ብሄር ሌሎች ብሄሮችን ሙሉ በሙሉ በብሄራዊ ጭቆና ስር ያስገባበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው፡፡

vii. ብሄራዊ የበላይነት በመሰረቱ የበላይነቱን ባረጋገጠው ብሄር ውስጥ ያሉ ገዢ መደቦችና በዝባዦች በጭቁን ብሄሮች ሰፊ ህዝብ ላይ የሚፈፅሙት ብዝበዛ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ግዜ ጀምሮ ብሄራዊ ጭቆና የመደባዊ ጥቆና አንድ አይነተኛ መልክ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይህ ጭቆና በአጠቃላይ በህብረተሰብ ዕድገት ላይ በተለይም ደግሞ የተረገጡ ብሄሮችና ህዝቦችን፣ ቋንቋቸውን ባህላቸውን፣ ታሪካቸውንና አጠቃላይ ማንነታቸውን በመግደል አድልዎን በማስፋፋት የብሄሮቹን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በመግታት ለከባድ ድህነትና ድንቁርና መሰረት በመሆን የህብረተሰብን ዕድገት ያደናቀፈ ሂደት ሆኖ በዓለም ላይ ታይቷል፡፡ ይህ ጭቆና አንደኛው ብሄር ሌሎችን በሃይል ስለሚጫንና ስለሚጨቁን የተፈጠረ ነው፡፡ ይህ ሊጠፋ የሚችለው ብሄሮቹ በጋራና በእኩልነት ያለ ጭቆና መኖር ወይንም ለየብቻቸው ተለያይተው የአንደኛው ብሄር ገዢ መደብ የሁለተኛውንና የሶስተኛው የሚጨቁንበት ዕድል ሲበጠስ ነው፡፡ተራማጅና ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች፣ የህዝብ ጠበቃ የሆኑት የእኩልነት ሃይሎች ብሄራዊ ጭቆና ባለበት ሁሉ ወይ በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ አንድነት ወይም የራስን ዕድል በራስ በመወሰን መገንጠል ብለው ነው የታገሉት፡፡ እኩልነት ከሌለ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ከብሄር መፈጠር ጋር አብሮ የተፈጠረ መብት ነው፡፡ ይህም በሰላማዊ መንገድ ወይም በሃይል የጭቆናው ሰለባ በሆኑ አገሮች በተለይ በምስራቅ አውሮፓ ብሄሮች ተፈፅሟል፡፡

### 2.1.2. የኢትዮጵያ አመሰራረትና ብሄራዊና የመደብ ጭቆና

i. የዛሬቱ ኢትዮጵያ እንደ አንዲት አገር በአፄ ምኒሊክ አገዛዝ ዘመን የተመሰረተች ናት፡፡ ከዛ በፊት በተለያዩ መሳፍንታዊ ግዛቶች የተከፋፈለችና ቀጣይነት ባለው የመስፍናውያን ወረራዎችና ግጭቶች ውስጥ የኖረች ስትሆን በሚኒሊክ አገዛዝ ግን የመስፍናውያን ወረራዎች ይዘት ተቀየረ፡፡ የዛሬዋ ኢትዮጰያ አፍሪካ በባዕድ ወራሪዎች በምትወረርበት ወቅት በምኒሊክ መስፍናዊ ወራር ወደ አንድ የተጠቃለለች አገር ሆነች፡፡ በዛን ጊዜ ቅኝ ገዚዎች ኢትዮጵያን ሊቆጣጠሯት ባለመቻላቸው ሚኒሊክ ከቅኝ ገዢዎች ያገኘውን ትጥቅና እውቀት ተጠቅሞ የተሻለ ወታደራዊ ተቋም ቢሮክራሲ ሊመሰረት በመቻሉ በተጨማሪ በቾኝ ገዢዎች መካከል የነበረውን ቅራኔ በመጠቀሙ፣ ወደ ምስራቅ፣ ደቡብና ምዕራብ ባደረገው ዘመቻ ሰራዊቱንና ቢሮክራሲው ሊሸከም የሚችል ኢኮኖሚያዊ ምስረታ በመፍጠሩ በተሟላ የወረራ ሂደት አንዲት ሉኣላዊት አገር ሊፈጥር ችሏል፡፡

ii. ይህ መስፍናዊ ወረራ በኢትዮጵያ አፈጣጠር ታሪክ ላይ ከባድ ጥፋት የተፈፀመበት ነው፡፡ ሚኒሊክ ወደ አራቱም አቅጣጫዎች ባደረገው ዘመቻ በህዝቦች ላይ ከፍተኛ ግፍና ጭፍጨፋ ፈፅሟል፡፡ በአንዳንድ አከባቢዎች የህዝቡ አንድ ሶስተኛ ያህል የተገደለበት፣ በሁሉም አከባቢዎች የተጠናከረ

ብዝበዛ የተተከለበት ህዝቦች መሬታቸው ሙሉ በሙሉ ተነጥቆ ጭሰኛ ሲሆኑ የሚኒሊክ ነፍጠኞች ግን የመሬቱ ባለቤቶች ሁነው እየመዘበሩ የሚኖሩበት፣ የህዝቦቹ እምነት፣ ታሪክ፣ ማንነት ሙሉ በሙሉ ተረግጦ ሰውነታቸውን እንዲዘነጉና ከእንስሳ በላይ ከሰው በታች ሆነው አጠቃላይ ሃብታቸው እንዲዘረፍና እንዲመዘበር የተደረገበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ የትግራይ ህዝብም በአስከፊ ግፍና ጭቆና ስር ወደቀ፡፡

iv. አንዲት አገርን በወረራ መመስረትና የካፒታሊስት ስርአት ማቆጥቆጥ በኢትዮጵያ ጐን ነጐን አልተጓዙም፡፡ በወረራው ጊዜ ምንም የካፒታሊዝም ጭላንጭል አልነበረም ባይባልም አገር በወረራ በምትፈጥርበት በዚያን ወቅት የካፒታሊዝም እድገት ገና አልጀመረም ነበር፡፡ በዘመቻው ወቅት የተሰበሰቡት ብሄረሰቦች ቆይተው ከካፒታሊዝም ካደገ በኋላ ወይ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ካልሆነም የራሰቸው ነፃ ብሄራዊ መንግስት እንዳይኖራቸው በተካሄደባቸው ዘመቻ በአማራ ገዢ መደብ እግር ስር እንዲወድቁ ተደርጓል፡ በማሕበረሰቡ ዕድገት ሂደት ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ እየተስፋፋ ሲመጣ በተለይም በሃይለስላሴ ግዜና ከጣልያን ወረራ በኋላ ትራንስፖርትና መገናኛዎች፣ ፋብሪካ፣ ንግድ ወዘተ እየተሻሻሉ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትስስር በመፍጠር በርከት ያሉ በሚኒሊክ በሃይል የተያዙ የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ወደ ብሄር ደረጃ የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

v. ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ካፒታሊዝም የተፈጠረበት አካሄድ በኣውሮፓ ከነበረው የተለየ ነበር፡፡ የአውሮፓ በተለይም የምዕራብ አውሮፓ ካፒታሊስትነት በውስጣዊ ሂደት የመጣ ሲሆን የኢትዮጵያ ካፒታሊዝም አመጣጥ ግን ከውስጥ የመጣ ሳይሆን ከውጭ በሊበራሊዝም ተፅእኖ የመጣ ነበር፡፡ ሊበራሊዝም የአገሪቷን ገዢዎች ይዞ የኢትዮጵያ ህዝብን መበዝበዝ እንዲቻል ስልጣን የያዙ መሳፍንትና ቢሮክራሲያውያንን ከብዝበዛው ተካፋይ በማድረግ መሳፍንት፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምና ሊበራሊዝም ቀንደኛ የብሄር ጭቆና ምንጭ ሆነው መጡ፡፡ ጭቆናውን ተቃውመው በሚነሱ ላይ ከባድ ጭፍጨፋ በማካሄድ በምኒሊክ ወቅት ከተፈፀመው ግፍና ወረራ ጋር ተደርቦ በተለየ ሁኔታ የከረረና መራራ ብሄራዊ ቅራኔና ጭቆና ተፈጠረ፡፡ ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ባህሪ እየያዘ መጣ፡፡ ይህ ብሄራዊ ጭቆና አብዛኛውን ማለትም 75 በመቶ የሚሆነውን ህዝብ ወደ መራራ ብሄራዊ ጭቆና ያስገባና ህዝቡን ከጭቆናው ለማላቀቅ በሚደረገው ትግል የተለየ ሚና የሚጫወት ሆነ፡፡ ከዛም አልፎ ብሄራዊ ጭቆናው የሚዘገንን ጭፍጨፋ አሰቃቂ ይዘት የነበረው ስፍር ቁጥር የሌለው የህዝብ ሞት ያስከተለ፣ ስደት፣ ድህነት፣ ድንቁርና አይን ያወጣ፣ አድልዎ የነገሰበት በአብዛኛው አከባቢ የህዝቡና የአገሪቷ የትግል ታሪክ ብሄራዊ መልክ በማልበስ ብሄራዊ ጥያቄና ብሄራዊ ትግልን በኢትዮጵያ አብዮት የተለየና ከፍተኛ ድርሻ እንዲይዝና ዋነኛው የመደብ ትግሉ ዋነኛ መግለጫ እንዲሆን ያደረገ ነው፡፡

## 2.2. የኢህአዴግ አሰላለፍ፣ ተልእኮ፣ ማሕበራዊ መሰረትና መለያዎች

I. የኢህአዴግን አሰላለፍ፣ መሰረታዊ ተልእኮና ማሕበራዊ መሰረቱን በተመለከተ ዋናው መነሻው ከላይ እንደ ኣጠቃላይ መነሻነት የተቀመጠው ጭቆናና ጭቆናውን ለመፍታት ታሳቢ ያደረገ ብሄራዊ ጭቆናን የማስወገድና የህዝብ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ትግል ነው፡፡ አሰላልፉን፣ ተልእኮውን ማሕበራዊ መሰረቱን ሁሉ የሚወሰነው ይህ መነሻ ነው፡፡ በዚህም መሰረት በዋነኛነት ኢህአዴግ የአርሶ አደሩን ጥቅም ለማረጋገጥ የቆመ ነው፡፡ ኢህአዴግ የጭቁኑ ሰፊ ህዝብ ድርጅት ነው ሲባል ከሁሉም በፊት ከሁሉም በላይ የአርሶ አደር ድርጅት ነው ማለት ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ኢህአዴግ በሃቅ የጭቁኑ አርሶ አደር ድርጅት ሊሆን ከሆነ እዚያው ሳለ የከተማ ጭቁን ህዝቦችን ጥቅምም ማስከበር አለበት፡፡ በዚህ መሰረት ኢህአደግ ለላብ አደሩና ለንኡስ ከበርቴውም የቆመ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ማለት ኢህአዴግ ዓላማውን ሲቀርፅ፣ ፖሊሲዎች ሲያወጣና አሰራሮችን ሲነድፍ ከሁሉም በፊት በላይ ችካል የሚያደርገው ገበሬውን መሰረት አድርጎ የከተማውን ህዝብ በማቀፍ ነው፡፡ ይህንን ተግባራዊ የሚደረገው ደግሞ በዚህ ዓላማ የሚጎዳውን ፀረ ለውጥ ኪራይ ሰብሳቢ ሃይል መታገል ብቻ ነው፡፡ የኢህአዴግ አሰላለፍ ይህ ነው፡፡

II. ኢህአዴግ አሰላለፉን የሚገልፅ እስትራተጂያዊ ተልእኮም የተሸከመ ነው፡፡ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማሕበራዊ መስኮች ተልእኮውን ግልፅ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ መጥቷል፡፡ በኢኮኖሚ በኩል በአክራሪ ኒዮ-ሊበራሊዝም ሰንሰለት ውስጥ ተሁኖ ሊመጣ የሚችል ፈጣን ካፒታሊስት ዕድገት በማምጣት የአገሪቱን ተነፃፃሪ የኢኮኖሚ ነፃነት በቀጣይነት ማጎልበት፤ የኢህአዴ ማሕበራዊ መሰረት የሆነው ህዝብ በስርዓቱ አጥር ውስጥ ሁኖ ሊያገኘው የሚችለውን የላቀ ጥቅም እንዲያገኝ፣ በፖለቲካ በኩልም የብርዥዋ ዴሞክራሲ ሙብቶችን ስርዓቱን አጥር ሳይሻገር በከፍተኛ ደረጃ መተግበር፣ ማጠንከርና ማስፋፋት፣ በዚሁም ህዝቡ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ እንዲሆን፤ በማህበራዊ ስራዎችም የማህበራዊ ፍትህ የሚያነግስ፣ የዜጎችን አቅም ግንባታ የሚያረጋግጥ የመሳሰሉት መተኪያ የሌላቸው ተልእኮዎችን የተሸከመ ድርጅት ነው፡፡

III. ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ከተሸከማቸው ተልእኮዎች አኳያ ሲታይ በአገራችን በጣም መሰረታዊና ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ሃላፊነት የተሸከመ ድርጅት ነው፡፡ ለመሰረታዊው ተልእኮ ድልም ትንሹ ሞተር ኢህአዴግ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለዘመናት ከቆየችበት የብሄር ጭቆና አላቆ በሱ ፈንታ በእኩልነትና በፍላጐት ላይ የተመሰረተ አንድነት በማምጣት ከመበታተንና መተላለቅ ሊያድናት የሚቻለው ዓለማና ተልእኮ የኢህአዴግ ነው፡፡ የኢህአዴግ ዓላማና ተልእኮ ከሌለ ለውጥ የለም፡፡ ለውጥ ከሌለ ደግሞ መበታተን የግድ ነው፡፡ የኢህአዴግ ተልእኮ ይህን ያህል የአገር መድህን የሆነ ዓላማ የተሸከመ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የኢህአዴግ ዓላማና ተልእኮ የኢትዮጵያን ህዝቦች መፃኢ ዕጣ ፈንታ በመወሰን

ያለው ድርሻ ተኪ የሌለው ነው፡፡ ይህንን በሚመለከት "የአብዮታዊ ዴሞክራስያዊ ስርዓት ምንነት" የተሰኘው መፅሓፍ ከገፅ 149 እስከ 150 ባለው እንዲህ ይላል፡፡

IV. "የኢህአዴግ ዓላማና ተልእኮ በዓለም ካሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የተለየ ድርሻ ያለው ነው፡፡ ብዙዎቹ ድርጅቶች አንድ እየተገነባ የቆየን ስርዓት የማስቀጠል ድርሻ ነው ያላቸው፡፡ እነሱ ኖሩ አልኖሩ በስርዓቱ ላይ የሚመጣ መሰረታዊ ለውጥ የለም፡፡ ስርዓቱ አስቀድሞ የተገነባ በመሆኑ እነሱ ባይኖሩም በሌላ ተተክቶ ይሰራል እንጂ በስርዓቱ ለ የሚመጣ ነገር የለም፡፡ የኢህአዴግ ዓላማዎች አንድ የተገነባ ስርዓትን ይዞ የማስቀጠል ሥራ አይደለም የሚሰራው፡፡ በአገራችን ያልነበረ ስር ነቀል አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት አዲስ ስርኣት ለመገንባት ነው እየተንቀሳቀሰ ያለው፡፡ የኢህአዴግ ዓላማዎች ይህን ለማድረግ ችሎታ ያላቸው ናቸው" ይላል፡፡

ከዚህ አንፃር ኢህአዴግ እስትራተጂካዊ ተልእኮቹ በጉልህ ያስቀመጠ፣ ከዚህ የሚመነጭ ትክክለኛ የመደቦች አሰላለፍ እና የህብረተሰቡ መደባዊ ትግል ሞተር ማንና የትኛውን መሆኑን ያነጠረና በተግባር መርቶ አስደናቂ ውጤት ያስመዘገበ ድርጅት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ የጀመረውን ከባድና መድህን የሆነ ተልእኮውን የሚያስፈፅም ባህርዩን ጠብቆ ይቀጥላልን ?

V. የኢህአዴግ ማሕበራዊ መሰረት በኢህአዴግ አሰላለፍ መሰረት የተቀመጠ መደብ ነው፡፡ ኢህአዴግ የአርሶ አደር ድርጅት ነው፡፡ የኃይሉ መሰረትና ምንጭ አርሶ አደርና በከተማ የሚገኝ የጭቁኑ ማሕበረሰብ ነው፡፡ የአርሶ አደሩ ድጋፍ የሌለው ኢህአዴግ የትም አይደርስም፡፡ በመሆኑም ከአርሶ አደሩ ርቆ ሳይሆን ከአርሶ አደሩ ተሳስሮና እርሱን ተሞርኩዞ የሚንቀሳቐስ ድርጅት ነው፡፡ ኢህአዴግን ልዩ ድርሻ እንዲጫወት የሚያደርገው ደግሞ ተልእኮው ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንስ ለዚሁ ተልእከው ለመፈፀም የሚያስችለው ማሕበራዊው መሰረት ስላለው ጭምር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ ከማህበራዊው መሰረቱ ጋር ያለው ግንኙነት በሰፊ ነፃነት ላይ የተመሰረተና ሞግዚታዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡

VI. አሁን ለኢህአዴግ ማሕበራዊ መሰረት የሆነው አርሶ አደር የመሬት ጥያቄው የተመለሰበት፣ ሰላም ያገኘ፣ ይብዛም ይነስም ራሱ የሚያስተዳድርና ዴሞክራስያዊ ጥያቄዎች የተመለሱለት፤ የድካሙ ውጤት ተጠቃሚ የሆነበትና መሬት አልባ በነበረበት ወቅት መሬት ለማግኘት በራሱ ተነሳሽነት ህዝባዊ እንቅስቃሴ የማድረግ ተጨባጭ ዓቅሙ ዝቅተኛ ነው፡፡ ዓበይት ጥያቄዎቹ የተመለሱለት ማሕበራዊ መሰረት ነው፡፡ ከተመለሱት ጥያቂዎች በማውጣት ወደ ከፍተኛ ተጠቃምሚነት፣ አብዮታዊነትና ትራንስፎርሜሽን ሽግግር ለመሻገር የሚያነሳሳው ኃይል ያስፈልገዋል፡፡ በራሱ ተነሳሽነት ወደዚህ የሚገባበት ሂደት ዘገምተኛ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኢህአዴግ ድርሻ ታላቅና ልዩ ይሆናል፡፡ አርሶ አደሩ ወደ ሽግግር (ትራንስፎርሜሽን) ለመግባትና ላለመግባት የኢህአዴግ ድርሻ ልዩ ነው፡፡ አርሶ አደሩ ይብዛም ይነስም እምነቱን በኢህአዴግ ላይ ጥሎታል፡፡ ኢህአዴግ አርሶ አደሩን አነሳስቶ ወደ

ትግል ካስገባው ግን አርሰ አደሩ የራሱን ተነሳሽነት አጠናክሮ ወደ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሊገባ ይችላል፡፡ ስለዚህ ኢህአዴግንና ማሕበራዊ መሰረቱን መገንዘብ ለኢህአዴግ ጉዞ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡

VII. በአጠቃላይ የነበሩ ኢህአዴግ አሰላለፍ፣ ተልእኮና ማሕበራዊ መሰረት ተደርገው የተቀመጡት ነጥቦች እዚያው ሳሉ መለያ እምነቶቹ ናቸው፡፡ የኢህአዴግ ተልእኮና ዓላማዎች ወገንተኝነታቸው ሙሉ በሙሉ አርሶ አደሩንና ገጠርን ማእከል ያደረገ ልማት ማረጋገጥ ዋናው መለያው ነው፡፡ ለዚህም ሲባል ሁሉንም ዓቅሞቹን አዋህዶ የሚጠቀም መሆኑ፤ የከተማ ህዝብንም ጭምር ከልማቱ ተካፋይ የሚያደርግ መሆኑ፣ በክልሎች መካከል የተመጣጠነ ዕድገት እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑ፣ በዲሞክራሲ መስከም በዋነኛነት የህዝቡን መብትና ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑ፣ የሰፊውን ህዝብ ሰፊና ቀጥተኛ ተሳትፎ ማረጋገጥና ማደራጀት በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በፀጥታና ዲፕሎማሲ፣ ዲሞክራሲያዊ አንፃራዊ አገራዊ ነፃነት ማረጋገጥ፣ ዲሞክሲያዊ አንድነት ማለትም የሁሉም ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ መብት የተረጋገጠበት የቡድን እና ግለሰብ መብቶችን በጋራ የሚተገብርና ይህንን መሰረት አድርጎ የሚፈጠር የህዝቦች አንድነት ባህላቸው፣ ታሪካቸው፣ ቋንቋቸው አጠቃላይ ማንነታቸው ማስከበርና እንዲጠቀሙ የሚያደርግ መብት፣ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ የሚሄድ መብትን ማስከበር ትምክህትና ጠባብነት አደገኝነታቸውን ለይቶ መታገል ነባሩ ኢህአዴግ በተልእኮውና በተግባራዊ ትግሉ የሚለይባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡

### 2.3. ተልእኮውንና መለያ እምነቶቹን የሚያስፈፅም ብቃት ያለው አደረጃጀት የተከተለ ድርጅት

#### 2.3.1. ብሄራዊ አደረጃጀትና የኢህአዴግ ግንባር በትጥቅ ትግል ወቅት

i. የኢትዮጵያንና የትግራይን ተጨባጭ ሁኔታ በሳይንሳዊ መነፅር ተንትኖ ትጥቅ ትግል የጀመረው ህወሓት/ኢህወዴግ አንደኛው ቁልፍ መለያው በብሄራዊ ጭቆናና አፈታቱ ላይ የወሰደው እርምጃ ነው፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ በዚያን ግዜ እና በኋላም የብሄር ጥያቄ፣ የራስ ዕድል በራስ የመወሰን መብት በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ የሚጫወተውን ድርሻና የአደረጃት መልክ በመምረጥ ረገድ የነበረው ልዩነት መደበኛ ይሁን ኢ-መደበኛ በብሄር ጥያቄ ሲንፀባረቅ የነበረው ውዥንብር ፈታኝ በነበረበት ሰዓት ዋነኛውን ቅራኔ ለይቶ የሚያታግል የአደረጃጀት አይነት የመለሰ ኃይል ነው፡፡ ህወሓት/ኢህአዴግ የብሄር ጥያቄ በዴሞክራስያዊ አብዮት ውስጥ የሚካሄድ መደባዊ ትግል አንድ ገፅታ መሆኑን በተለይ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ደግሞ የመደብ ትግሉ አንድ ገፅታ ብቻ ሳይሆን ዋነኛው የመደብ ትግል መግለጫ መሆኑን በመገንዘብ የትግሉ አደረጃጀትም ከዚህ እንደሚነሳ በሚገባ ያሳየና ተግባራዊ ያደረገ ድርጅት ነው፡፡

ii. ብሄራዊ ጭቆና ብሄራዊ ትግል በዚያን ጊዜ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ በአጭርና በተቀላጠፈ መንገድ የሚያንቀሳቅስ የበለጠ የትግል መስመር ሁኖ ብሄራዊ ጭቆናን ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ህዝቡን በሚሰማውና በግልፅ በሚታይ አስካፊ ጭቆና፣ የህዝቡ የትግል ተመክሮ በብሄራዊ ትግል ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ህዝብን በማነሳሳት ለሙሉ መደባዊ አርነቱም ጠንካራ መሰረት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ደግሞ ብሄራዊ ጥያቄና ትግል እንዲሁም ብሄራዊ አደረጃጀት በኢትዮጵያ አብዮት ከፍተኛ ቦታ የተያዘበት፤ በብሄራዊ ጭቆናና በደል የማይነሳሱት ደግሞ በህብረ ብሄራዊ አደረጀጀት የሚታገሉ በድምሩ የብሄር ጥያቄ ብሄራዊ አደረጃጀት እንደ ዋንኛ የመደብ ትግል መንገድ፣ እንደ የዴሞክራስያዊ አብዮት የድል መንገድ በትክክል አስቀምጦ በመታገሉ በህዝብ ዘንድ ፅኑ መሰረት ያለው አብዮታዊ ትግል እንዲካሄድና እንዲሳካ አስችሎታል፡፡

iii. በዚያን ጊዜ ብሄራዊ ቅራኔና በብሄራዊ አደረጃጀት ላይ የተመሰረተ መስመር አስፈላጊነቱ ትግል ኣብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ በብሄራዊ አደረጃጀት በአፋጣኝና በአጭር ጊዜ ያንቀሳቀሰ ነበር፡፡ ይህም የበለጠ የትግል መስመር ሆኖ ብሄራዊ ጭቆና ለማጥፋት ብቻ ሳይሆን ህዝቡን በሚሰማው መራራ ጭቆና ከህዝቡ የትግል ተሞክሮ አንፃር በብሄራዊ ትግል ላይ የተመሰረተ የነበረ መሆኑ በማንሳት መላው መደባዊ ነፃነቱም ጠንካራ መሰረቱ እንዲሆን ተደረገ፡፡  ስለዚህ ጥያቄና ትግል ብሄራዊ አደረጃት በኢትዮጵያ አደረጃት ላይ ከፍተኛውን ቦታ የያዘበት በብሄራዊ ጭቆና የማይነሱ ደግሞ በህብረ ብሄራዊ አደረጃት የሚታገሉበት በድምሩ የብሄርና ብሄራዊ አደረጃት ጥያቄ እንደ ዋንኛ መደባዊ ትግል እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በትክክል አስቀምጦ መታገሉ በህዝብ ዘንድ ፅኑ መሰረት ያለው አብዮታዊ ትግል እንዲያካሂድና ለድል እንዲበቃ አስችሎታል፡፡

iv. ብሄራዊ ትግልና በብሄራዊ አደረጃጀት ላይ የተመሰረተ መስመር አስፈላጊነቱ እንደታየ ሁሉ አጠቃላይ የትግል ስትራተጂና ስልት ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ አብዮት ጋር የሚኖረው ዝምድና መለየት አስፈላጊ ነበር፡፡ በብሄራዊ ትግሎች መካከል እርስ በርስም ሆነ በብሄራዊና ህብረ ብሄራዊ ትግሎች መካከል ሊኖር የሚገባውን ዝምድና ማጠናከርና ማንጠር በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ሌላኛው ከፍተኛ ትርጉም  የነበረው ጥያቄ ነበር፡፡ በመሆኑም የተለያዩ የትግል አደረጃጀት በመያዝ በጋራ ዴሞክራስያዊ ዓላማዎች ዙርያ የጋራ ስትራተጂያዊ ግንባር መፍጠር አስፈላጊ ነበር፡፡ ቀድሞ ነገር የኢትዮጵያ ዴሞክራስያዊ ኃይሎች በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት በአንድ ድርጅትና በአንድ መፈክር ስር ተሰባስበው ሊታገሉ ስለማይችሉ ፣ የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በተለያዩ  አከባቢዎች በተለያዩ ደረጃዎች የተካረረና በዚህም መሰረት የተለያዩ መፈክሮችን ያነገቡ ዴሞክራስያዊ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ የሚጋብዝ ነበር፡፡

V. ይህ ከማንኛውም ኃይል የግል ፍላጎት የሚመነጭ ሳይሆን በኢትዮጵያ ከሚገኙ ቅራኔዎች ተፈጥሮና የመካረር ደረጃ የሚመነጭ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ህዝቡን በቀላሉ እንዲታገል የሚያስችለው ዴሞክራስያዊ መፈክርና አደረጃጀት፣ በሌላ በኩል ያለውን ህዝብ በአግባቡና በፍጥነት ሊያነሳሳው የማይችል ነበር፡፡ በመሆኑም በየአከባቢው ህዝቡን በበለጠ የሚያታግል ዴሞክራስያዊ ዓላማና ድርጅት መፈጠሩ የግድ ነበር፡፡ አንድ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ብቻውን የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያውያን ኃይሎች በሚገባ አሰባስቦ ለመታገል የሚያስችለው ነባራዊ አደረጃጀትና የቅራኔዎች መካረር በኢትዮጵያ አልነበረም፡፡

ይህን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያውያን ኃይሎች በብሄሮችና ህብረ-ብሄሮች የተለያዩ አደረጃጀቶችና መፈክሮች እንዲበታተኑ የግድ የሚያደርገውን ሁኔታ የሚፈታ ስትራተጂካዊ ግንባር መፍጠር ለብሄራውና መደባዊ ድልና አርነት እንዲሁም በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ አንድነት ለመፈጠር የኢህአዴግ እንደ ግንባር መመስረት ጉዳይ አማራጭ ያልነበረው ሁኔታ ነበር፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ አብዮት የሞት የሽረት ጥያቄ ነው የነበረው፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የብሄራዊ ድርጅትና በርሱ ላይ የተመሰረተ ግንባር አስፈላጊነት መሰረታዊ ይዘት ይህ ነበር፡፡ ይህ አደረጃጀት የዴሞክራስያዊ አብዮት ጠላቶችን ደምስሶ በህዝባዊ መንግስት ምስረታ ድል ተጠናቋል፡፡

### 2.3.2. ከድል በኋላ የቀጠለው የኢህአዴግ አደረጃጀትም ተገቢ ነው!

I. ዴሞክራስያዊ አብዮቱ ያስቀመጠው ተልእኮ በታሪካዊ ድል እንዲሁም ወርቃዊ ሕገ- መንግስትና የህዝባዊ ስልጣን ምስረታ ከተጠናቀቀ በኋላ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የቅራኔ ለውጥና ዕድገት መጥቷል፡፡ ብሄራዊ ጭቆናና ብሄራዊ ጥያቄ ዋነኛው የመደባዊ ጭቆና ገፅታና ዋነኛ የትግል መልክ ሆኖ የቆየ ሲሆን በህዝባዊ ትግልና አፈታት ሂደት የብሄር ቅራኔ የብሄሮች ራስን በራስ የመወሰን መብት በማረጋገጥ ህዝቦች በፍላጎታቸው እንዲተባበሩ በማድረግ ወይም የመገንጠል መብታቸውን ተጠቅመው ነፃ መንግስት እንዲመሰርቱ በማድረግ ይጠቃለል በሚል ዘላቂና ወሳኝ መቋጫ፣ የብሄራዊ ጭቆናው መሰረት የነበሩ ጠላቶችን በመደምሰስና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ሕገ-መንግስታዊ ዋስትና ካገኘ በኋላ ብሄራዊ ጭቆና ተወግዷል፡፡

II. ይህም በመሆኑ የብሄር ጭቆና በሌለበት የብሄር ቅራኔ ዋነኛ የቅራኔዎች ገፅታ ሊሆን አይችልም፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ዋነኛው ቅራኔ መደባዊ ቅራኔ ሁኖ ነው የመጣው፡፡ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ ዋነኛ ሞተር ሆኖ የሚያንቀሳቀሰው የመደብ ትግል በአንድ በኩል አብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች በሌላ በኩል ደግሞ ጥገኛ ክራይ ሰብሳቢ ኃይሎችና ዓለማቀፍ ሰንሰለታቸው የተሳተፉበት ዋነኛ ፍልምያ ነበር፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮ ብሄራዊ ቅራኔ ለመደባዊ

ቅራኔን የሚሸፈንበት ሂደት ተቋርጧል፡፡ እንዲህ የመሰለውን ለውጥና እድገት መሰረት አድርጎ ኢህአዴግ የመደብ ትግሉ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ የሚኖረውን ተልእኮ፣ አሰላለፍ፣ የሚገጥመው አደጋና አመካከቱን በተሃድሶ ለይቶ ትግል እያካሄደ ቆይቷል፡፡ የአደረጃጀት ለውጥ ግን አላደረገም፡፡ በብሄራዊ ድርጅቶች ላይ የተመሰረተ የኢህአዴግ ግንባር ነው የቀጠለው፡፡ ለምን?

III. ከላይ የተቀመጠው የቅራኔ ለውጥና ዕድገት እንዳለ ሆኖ ብሄራዊ ጭቆና በሌለበት ብሄራዊ የአደረጃጀት ገፅታ ቀጥሏል፡፡ ይህንን በሚመለከት ታላቁ የድርጅታችን መሪ የነበረው ታጋይ መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ የፓርቲ ጥያቄዎች ላይ የተሰጠ አስተያየት በሚለው ያልታተመ መፅሓፍ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡፡

"ብሄራዊ ቅራኔ በሌለበት የብሄር ቅራኔ በምንም ተአምር ዋነኛው ቅራኔ ሊሆን አይችልም፡፡ አሁን ዋነኛው ቅራኔ የመደብ ቅራኔ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ጠባብነትና ትምክህት አሉ ብቻ ሳይሆን፣ ጠላቶች ናቸው ብቻም ሳይሆን በሚያሳስብ ሁኔታ እየጎለበቱ እየሄዱ ናቸው፡፡

ብሄራዊ ጭቆና በተወገደበት፣ መሰረታቸው በጠፋበት በዚህ ዘመን እነዚህ በሽታዎች ከየት ይበቅላሉ? ማተርያላዊ መሰረታቸው ምንድ ነው? በመደብ ባህርያቸውስ የት ይመደባሉ የሚለው ሊዳሰስ ይገበዋል፡፡ የህዝቦች ብሄራዊ መብት ቢረጋገጥም እንኳ ህዝቦች በዚህ መብት የመጠቀም ችሎታቸው ግን በታሪክ እንደተወረሰው ቀጥሏል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ይህንን በሚገባ አላጠበበውም፡፡ ስለዚህ ይህ ነባራዊ ልዩነት የጠባብነትና ትምክህት ዋነኛው ማቴሪያላዊ መሰረት ነው" ይላል፡፡

እዚህ ላይ የተገለፀው መሰረታዊ ነገር ብሄራዊ ጭቆና ከመወገዱ ጋር ተያይዞ ትምክህትና ጠባብነት ያላቸው ማተርያላዊ መሰረትና አደገኝነት ለውስጠ ድርጅት የመደብ ትግል፣ እንዲሁም በህብረተሰቡ መደባዊ ትግል አደረጀጃትና አሰራር ላይ የሚኖራቸውን ትርጉም ከዚህ እየተነሱ ማየትና መዘርዘር አስፈላጊ ነው፡፡

IV. ጥገኞች በድርጅት ውስጥም ሆነ በህብረተሰብቡ ውሰጥ የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማረጋገጥና የህዝቡን የልማት ጥማት በማርካት የህዝብ ድጋፍ ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ዓላማቸው ሸቀጦችና አገልግሎቶች በገበያ ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋና ጥራት በማምረት እየሸጡ ክብር ማግኘት ሳይሆን የመንግስትን ስልጣን በመያዝ ወይም ስልጣን ላይ ተመሳጥረውና ዘርፈው በአቋራጭ ራሳቸውን ማበልፀግ ነው፡፡ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት ዴሞክራስያዊ ስርዓት ተግባራዊ ከሆነ የመንግስት ስልጣንን ተጠቅመው የህዝብና የመንግስት ንብረት እየዘረፉ ሃብት ሊያካብቱ አይችሉም፡፡ ስለሆነም በባህርያቸው ፀረ- ዴሞክራሲ፣ ፀረ- ልማትና ፀረ- ህዝብ ናቸው፡፡ ህልውናቸውን ለማረጋገጥ ግን ቀጥተኛ ይሁን ቀጥተኛ ያልሆነ የህዝብ ድጋፍ ደግሞ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በተጨባጭ ፖለቲካዊ አቋማቸውና ተግባራቸው የህዝብ ድጋፍ ማግኘት ስለማይችሉ ሙሉ በሙሉ በትምክህትና ጠባብነት ገመድ ይንጠለጠላሉ፡፡ የአንድ ብሄር የመደብ

ክፍፍል በማድበስበስ "ደማችንን አንድ ነው፣ የወንዜ ጅብ ይብላኝ" በሚል መፈክር በቀጥተኛ ይሁን ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የህዝብ ድጋፍ በማግኘት የመንግስት ስልጣንን ለመያዝ ይሞክራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ትምክህትና ጠባብነት ህዝብን ከጥገኞች የሚያስተሳስሩ የጥገኞች ምርጥ ገመዶች ይሆናሉ፡፡

V. በዚህ መሰረት ትምክህትና ጠባብነት ጥገኞች ስልጣን ይዘው እንደፍላጎታቸው እንዲዘርፉና እንዲያልቡ እንደ መሰላል የሚጠቀሙበት ፍቱን አመለካከት ነው፡፡ እንደ ጥያቄና መፈክር መጠን የጥገኞች ጥያቄና መፈክር ነው፡፡ ሙስናና ፀረ ዴሞክራሲ ባሉበት ሁሉ ጥገኝነትና መለያው የሆኑት ትምክህትና ጠባብነት ይኖራሉ፡፡ በሙስናና ፀረ ዲሞክራሲ የሚገልፀው የድርጅታችን የመበስበስ አደጋ በየጊዜው በሚመጣበት ወቅት የሚታየው በብሄር ውስጥ በመደብ ክፍፍል ወገን ለያቶ በመታገል ፈንታ "ደማችን አንድ ነው" በሚል መፈክር ተሸፈነው በውጭ ካሉት ጥገኞች ጋር ራሳቸውን በማደላደል ራሳቸውን ወደ ጥገኛ ገዢ መደብነት የማሸጋገር ሂደት ነው እየታየ የመጣው፡፡ ለዚህም ነው ጠባብነትና ትምክህት የጥገኞች መበስበስ አደጋ ዋነኛ ፖለቲካዊ መገለጫ ሆኖ በየጊዜው የሚታየው፡፡

VI. አዲስ ጥገኛም ሆነ ገዢው የመደብ ቅሪቶች የጥገኝነት ተልእኮና ዓላማ አንግበው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ መደባዊ መሰረት ጠባብነትና ትምክህተኝነት ነው፡፡ ስለሆነም በየአከባቢው፣ በየብሄሩ፣ ያለው ጥገኛ ነው ትምክህትንና ጠባብነትን ሲሰራና ሲያቀጣጥል የቆየው፡፡ ስለሆነም የእነዚህን አስተሰባቦች ማተርያላዊ መሰረት በማጥፋት በመብት አጠቃቀም ያለውን ነባራዊ ልዩነት የሚያጠብ ብቁ እንቅስቃሴ በማድረግ ዋነኞቹን የጥገኝነት አንቀሳቃሾች በመታገል፣ በመደብ ትግል አማካኝነት ብቻ ነው ድል ማድረግ የሚቻለው፡፡ ይህ የሚካሄድበት አገባብና ሂደት ደግሞ በየአከባቢው፣ በየብሄሩ ጥገኞችን በመታገል ብቻ ነው ትምክህትንና ጠባብነትን ማዳከም የሚቻለው፡፡ እነዚህን አመለካከቶች ሁሉም በያለበት ሊዋጋቸው የሚገባ ቢሆንም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተልእኮ ተጨባጭ ብሄራዊ ማንነት መሰረቱና ማዕከሉ ያደረገ የየራስህን ጥገኛ ራስህ መታገል ነው ወሳኝ የሚሆነው፡፡ የመደባዊ ትግሉ መሰረቱና ማዕከሉ ራስህን ወደ ጥገኛ ገዢ መደብ ለማሸጋገር ሲባል የነዚህ አስተሳሰቦች ተሸካሚና አራማጅ ላለመሆን በቆራጥነት መታገል ነው፤ ዋናው ጉዳይ፡፡

VII. ስለሆነም በብሄራዊ አደረጃጀት ላይ የተመሰረተ የኢህአዴግ ግንባር ይህንን ተልእኮ ለመፈፀም የተሻለ ዕድል የነበረውና ያለው አደረጃጀት ነው፡፡ በትምክህተኝነት የሚገለፅ ጥገኛ መበስበስን ለመታገልና ለማዳከም ይህንን ተልእኮ የተሸከመ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ብሄራዊ ድርጅት ከፍተኛ ብቃትና ውጤት አለው፡፡ በጠባብነት የሚገለፅ ጥገኛ መበስበስን ለመታገልም እንዲሁም፡፡ በሙብት አጠቃቀም ዙርያ ያለውን ነበራዊ ልዩነት ለማጥበብ በሚደረገው ትግልም የበለጠ ውጤት የሚያመጣው በየብሄሩ ያለውን ዕንቅፋት ለይቶ በመታገል ነው፡፡ ህዝብን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዙርያ በማሰለፍ የጠራ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እና አስተዳደር ተከትሎ ራስን ወደ ጥገኛ ገዢ

መደብ የሚያሸጋግረውን ሂደት ዘግቶ ትምክህትና ጠባብነት ምንም ዓይነት መደባዊም ሆነ ፖለቲካዊ መሰረት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ብሄራዊ አደረጃጀት የተሻለ ዕድል የሚሰጥ እንጂ ራሱ ችግር አይሆንም፡፡

ችግሩ በአጠቃላይ ጥገኛ መበስበስን በተለይም በትምክህትና ጠባብነት የሚገለፅ ጥገኝነትን ለይቶ በመታገል ላይ በተለይም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመራር ባህሪ መጠበቅ፤ የጥገኝነት ኢኮኖሚያዊ መሰረት የማድረቅ ትግል ማዳከም ነው፡፡ አሁን በኢህአዴግ ውስጥ ያጋጠመው የጥገኛ መበስበስ አደጋም ዋነኛ ፖለቲካዊ ገፅታው ጠባብነትና ትምክህት አደጋ ነው፡፡ አሁን በስልጣን ያለው ጥገኛ ኃይልም ራሱ አሁን ስልጣኑ እያንገዳገደው የሚገኘው ይህ ፅንፈኛ ብሄርተኝነት ዋነኛው አደጋ እንደሆነ (በፍፁም ኤክስተርናላይዜሽን) ተገዶ ጭምርም በፅሑፎቹ እያነሳው ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ በኢህአዴግ የሚተዳደር አከባቢም ሆነ ታዳጊ (ኢጋር) ክልልች ላይ በአመራር ብቃት ማነስ የተፈጠረ ልዩነት እንጂ የኢህአዴግ አደረጃጀትን በነበረው ቦታ ሊያስቀጥል የሚያስችል ሁኔታ መኖሩን መገንዘብ ይገባል፡፡

VIII. ከኢህአዴግ አደረጃጀት ጋር ተዛምዶ ሲነሳ የቆየውና አሁንም ያለው ሌላ ጉዳይ በታዳጊ ክልሎች የሚገኙ በኢጋር ድርጅቶች የብሄረሰብ ድርጅቶች ለምን የግንባሩ አባላት አልሆኑም? በሚል የሚነሳው ነው፡፡ ጥያቄው ትክክለኛውና አግባብነት ያለው ነው፡፡ በነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ መሬት ተከፋፍሎ የሚኖር አርሶ አደር አልነበረም፡፡ የህዝቡ የኑሮ መሰረት እንስሳትን በማራባትና በመከተል ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በዚህ ኑሮ የተመሰረተ ጠንካራ የነገድና የጎሳ ትስስር ያለው ነው፡፡ ይህ ነው የሚባል የመደብ ቅራኔ አልነበረም፡፡ መሰረታዊ የፖለቲካ ትስስርም በስጋ ወይም በደም ዝምድና የተመሰረተ ነው፡፡ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የጐሳ መሪዎች ናቸው የሚያስተዳድሩት፡፡ በመሆኑም በዚነህ አከባቢዎች ከመስፍንነትና አርሶ አደር ቅራኔ በተለየ ጐሳዊ ትስስር የጎለበተ በመሆኑ ከዚያም አልፎ በገጠሩ ትርጉም ያለው የጠነከረ የመደብ ትግል ባለመኖሩ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል መሰረት የሚሆን መቆናጠጫ መደብ አልነበረም፡፡

IX. እንዲህ ያለ ሁኔታ መገለጫ በሆነበትና ሁኔታውን ሊሸከም የሚቻል መደብ ባልነበረበት ጥቃቅን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አካላት ሊገኙ ይችላሉ፤ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ድርጅት ግን በዚህ አከባቢ ሊኖር አይችልም፣ አልነበረምም፡፡ ስለሆነም አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መሪ መፍጠር አይቻልም ነበር፡፡ በመሆኑም ባለፉት ዓመታት በአደረጃጀት ደረጃ የግንባሩ አባላት ሊሆኑ አይችሉም ነበር፡፡ ሊደረግ የሚችለውና የተደረገውም ምንም ቢሆን እንኳ ውጤቱ በሚፈለገው ደረጃ ባይፈፀምም እነዚህን አከባቢዎች ኢህአዴግ በቀጥታ አነሳስቶ ሊያንቀሳቅስ እንደማይችል በመገንዘብ በአካባቢው በሚገኙ መሪዎችና ምሁራን በዓቅም ላይ የተመሰረተ ፖለቲካና ድርጅት እንዲሁም ሰፊ የልማት ስራዎች በማካሄድ መሰረቱ እንዲለወጥና ተጠቃሚነታቸው እንዲያድግ፤ ከሌሎች አከባቢዎች ጋር ያላቸው ልዩነት እንዲጠብ ለማድረግ ተሞክሯል ሩቅ ግን አልሄደም፡፡ በሂደት የጎሳ መሪዎችን

በማሳተፍ አፈፃፀሙን ለመሻሻል የተሄደውም ጭምር ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ በመሰረቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ልዩ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ችግሮችን በማጥናት ከህዝቡ ጋር በመመካከር የተጠቃሚነት ሙብታቸውን ማሻሻል ይቻል ነበር፡፡ ይህ ዕቅድ ግን በሚፈልገው መጠን እንዳልሄደ ማስቀመጥ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ጉዳይ የነበረው ጉድለት ነው ጥርት ባለ መንገድ ሊቀመጥና ሊወሰድ የሚገባው፡፡ የግንባሩ አባሎች ሆነው አለመቆየታቸው ግን ተገቢና ትክክለኛ ነው፡፡ በአጠቃላይ ኢህአዴግ ሲከተለው የነበረው ብሄራዊው አደረጃጀት በሁሉም ገፅታው ተገቢና ምክንያታዊ ነበር ብሎ መደመደም ይገባል፡፡

## 2.4. አንፀባራቂ አገራዊ ለውጥ ያረጋገጠ ዓላማና አደረጃጀት

I. ማንኛውም ዓላማና ማስፈፀምያ አደረጃጀት ከነችግሩም ቢሆን ባስመዘባቸው አንፀባራቂ ድሎች ነው ሊመዘን የሚገባው፡፡ በዚህ መሰረት የኢህአዴግ ተልእኮና አደረጃጀት ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ የተጓዘው ከነ ትላልቅ ድክመቶቹ አንፀባራቂ ድሎችን አስመዝግቧል፡፡ በኢኮኖሚ ዙርያ ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ 8 በሙቶ ባለፉት 15 ዓመታት ደግሞ 10 በሙቶ የኢኮኖሚ እድገት ሲያስመዝግብ ከ500 ዓመታት በላይ በከባድ የቁልቁለት ጉዞ ላይ የነበረችውን አገር ጉዞ በመግታት ወደ ተሻለ ከፍታ ያስጓዘ፤ በታሪክ ከነ ኮርያ፣ ታይዋንና ቻይና ረድፍ የሚመደብ፣ እድገት ብቻ ሳይሆን ተጠቃሚነትንና ፍትሓዊነትን በተሻለ በገጠር በአርሶ አደሩ፣ በከተማ ደግሞ በተለይ በዝቅተኛና በመከካለኛው የኑሮ ደረጃ የሚገኝ ማሕበረሰብ ዘንድ ጉልህ ለውጥ ተመዝግቧል፡፡

II. በማሕበራዊ ልማትም ይህ ነው የሚባል የትምህርት መስፋፋት ያልነበራት አገር አሁን 30 ሚልዮን የሚጠጉ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ የሚገኙባት አገር፤ በሙቶዎች የሚቆጠሩ ኮሌጆችና የማስልጠኛ ተቋሞች፣ በአስሮች የሚቆጠሩ ዩኒቨርስቲዎች፣ በአጠቃላይ የዜጋውን መሰረት የሚቀይር ስራ ነው የተሰራው፡፡ በጤና በኩልም በሽታን በመከላከል ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ ተነድፎ በ1982 ዓ/ም አንድ ሰው በህይወት የሚቆይበትን በአማካይ 45 ዓመት የነበረውን ዕድሜ በ2008 ዓ/ም ወደ 65 ዓመት ያደረሰ በኢኮኖሚ መሰረተ ልማቶችም በብዙ የዓለም አገሮች ባልተለመደ ሁኔታ ከጥዋቱ ጥራቱን የጠበቀ ፖሊሲ በመንደፍ በመንገድ፣ በኃይል ማመንጫ፣ በመገናኛዎች፣ ባቡርና ሌሎች ሜጋ ፕሮጀክቶች ጉልህ እንቅስቃሴ ተደርጓል፡፡

III. ሲጀምር ሰላምና መረጋጋት ያመጣ፤ ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን የጦርነት አውድማ የነበረችውን አገር፤ በአንዲት ጀምበር በሺዎች የሚቆጠሩ የሚሞቱባት የነበረችውን አገር ችግሩን ከምንጩ የሚያደርቅ የሰላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ አጀንዳዎች በማቀጣጠል የውስጥ ሰላምን ከማስጠበቅ አልፎ ለአጎራባች አገሮችም የሰላም ሃዋሪያ የሆንበት በዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ትላልቅ መሰረቶች የተጣሉበት የፀረ- ዴሞክራሲና አሃዳዊ ስርዓትን ያፈራረሰ፤ የአገሪቱን መሰረታዊ ችግሮች የሚፈታ ምርጥ ሕገ -መንግስት፤ ብሄራዊው ጭቆናን ከምንጩ የሚያስወግድ፣ ከፀረ-

ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያዊነት ወደ ዴሞክራሲያዊ በእኩልነት ላይ የተመሰረተች አዲስ ኢትዮጵያዊነት ያሻጋገረ፤ አገሪቱን ከብተና ያዳነ፣ የህዝብን ዴሞክራሲያዊ፣ ቀጥተኛና የተደራጀ ተሳትፎ ያጎለበተ፣ የህግ የበላይነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያላት የአገር ምስረታን ያስጀመረ ነው፡፡

IV. ዓለም አቀፍና አከባብያዊ ግንኙነቶችና ትስስሮችን በመሰረቱ የለወጠ፣ ከቅርብ እስከ ሩቅ አገሮች፣ ከወደቁ እስከ ሃያላን መንግስታት ተቀባይነት ያለው ግንኙነት ያጠናከረ፤ ጠላት የማይፈጥር ዲፕሎማሲ፣ ድህነትና ኋላቀርነትን ቀንደኛ ጠላት አድርጎ የፈረጀ፤ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲውን ከውስጥ ወደ ውጭ የሚያይ፤ የጋራ ተጠቃሚነትንና የአገሮች ሉኣላዊነት የሚጠብቅ፣ በዚህም ከአውሮፓ ሕብረት እስከ የአሜሪካ መንግስታት፣ ከሩስያ እስከ ቻይና፣ ከጃፓን እስከ ኮርያ፣ ከመካለኛ ምስራቅ እስከ ደቡብ አሜሪካና አውስትራልያ በመደጋገፍ፣ በጋራ ጥቅምና መከባበር ላይ የተመሰረተ ዲፕሎማሲያዊ ድሎች- - - ወዘተ ተመዝግበዋል፡፡

V. በሌላ መልኩ ሲታይ ትላልቅ ሁለገብ ዕድገቶች ተመዝግበዋል፡፡ ይህች አገር ከዝቅተኛ ደረጃ ተነስታ ያለመቋረጥ ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ እየተሸጋገረች መጥታለች፡፡ በዘመነ ግሎባላይዜሽን ሁሉም አገሮችና ህዝቦች ህልውናቸውን በቀጣይነት የሚያረጋግጡት በማያቋርጥ የዕድገት ጎዳና እስከ ተጓዙ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ከተንሸራተቱ ግን ውጤቱ ሁከት፣ ብጥብጥና መበታተን መሆኑን የተገነዘበው ኢህአዴግ በዚህ ከባድ የፉክክር ዓለም ይቅርና በድህነት ውስጥ የሚገኙ ያደጉ አገሮችም የሚናወጡበት ግሎባላዜሽን ይቺን አገር መርቶ በፈጣን የዕድገት ሃዲድ ስላስገባት የግሎባላይዜሽንን ማዕበል በተሻለ ደረጃ እንድትቋቋመውና እንድትከላከለው አድርጓል፡፡ ይህ የሆነባቸው ወሳኝ ምክንያቶች ደግሞ ከሁሉም በፊት ኢህአዴግ የሚመራበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ መሆኑ፤ የጠራ ስነ ሃሳባዊና ፖለቲካዊ አደረጃጀት ብቃት ባለው መንገድ ታጥቆ የሚመራው መሆኑ፣ በተጣራ ስትራተጂካዊ አሰላለፍ፣ ታክቲክና መለያ እምነቶች ላይ ሆኖ ጠንካራ የአስተሳሰብ እና የተግባር ዲሲፕሊንና አንድነትን በሚያረጋግጡ መርሆዎች መምራቱ፣ ራሱን በራሱ ጠንካራ የመደብ ትግል በማካሄድ ድክመቶቹን የሚያርም ፈተናዎችን የመሻገር ብቃት፣ በከፍተኛ የህዝብ ውግንና ያለው ህዝቡን በዙርያው በማነሳሳት፣ በማደራጀትና በመንቃት የህዝብ ወሳኝነትን አጥብቆ በመያዝ የተጓዘ ድርጅት በመሆኑ ነው፡፡**አሁንስ?**

**1. በኢትዮጵያዊያ አገር አቀፍ የተዋሃደ አንድ ፓርቲ ምስረታ ጥያቄ**

**1.1. መነሻ**

I. አደረጃጀት ማለት ሰዎች ወይም የማህበረሰብ ክፍሎች ተመሳሳይ የሆኑ ፍላጎታቸውንና ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ፣ የአጭርና የረጅም ግብ ነድፈው፣ ይህን ለማሳካት የሚያስችላቸው አቅጣጫዎች ቀይሰው አደረጃጀቱ የሚመራባቸውንና የሚተዳደርባቸውን የጋራ መርሆዎችና ደንቦች በመቅረፅ የሚያቋቁሙት የጋራ ፍላጎት ማስፈፀምያ መሳርያ ነው። በመሰረቱ አደረጃጀት የነዚህን የጋራ መሰረታዊ ፍላጎቶች ማስፈፀምያ ታክቲክ ነው። እነዚህን የጋራ ግቦች የሚያስፈፅም የዛሬና የነገ አደረጃጀት ሊለዋወጥ ይችላል። በዚህም መሰረት ይህንን ፍላጎት የሚያስፈፅም አደረጃጀት ከተጨባጩ ንኡስ መድረክ ጋር የሚበለፅግና

በነባራዊ ሳይንሳዊ ትንታኔ ተመርኩዞ በየወቅቱ የሚፈፀምና የሚለዋወጥ ነው። ከዚህ አንፃር በኢህአዴግ ውስጥ የአደረጃጀት ጥያቄ መነሳቱ በጥቅሉ ስህተት አይደለም። ከዚህ በተጨማሪም ቀደም ብሎም ኢህአዴግ ሊኖረው የሚገባውን የአደረጃጀት እድገት አንስቶ ውይይት ሲያደርግበት የመጣ ጉዳይ ነው። በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ያለው የሊግ ኣደረጃጀት ለቀጣይ የኢህአዴግ አደረጃጀት ምን ምልክቶች ይሰጣል በሚል የተነሳው ዓይነት የሚታወስ ነው። ስለዚህ በኢህአዴግ መድረኮች የኢህአዴግ የአደረጃጀት ለውጥ ጥያቄ ተነስቶ ተጠንቶ እንዲቀርብ ህወሓት የተስማማው በዚህ ምክንያት ነው።

II. አደረጃጃት ከወቅታዊ ሁኔታና ንኡሳን መድረኮች ጋር እየተዛመደ የሚለዋወጥ ታክቲክ (ስልት) ነው ሲባል ግን ተራ የቴክኒክ ጉዳይ በፍፁም እንዳልሆነ መታወቅ ኣለበት። የአመለካከት አንድነት ብቁ በሆነ የአደረጃጀት ጥንካሬ አንድነት ካልታጀበ ወደ ተግባር አንድነት ተቀይሮ ቁሳዊ ሃይል ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም በአጠቃላይ አደረጃጀት በተለይ ደግሞ ውህደትና ግንባር ወደ አንድ የመምጣት ጉዞ ላይ በዋነኝነት የአደረጃጀት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ገዢ ሃሳብ ነው። ምን ዓይነት የአደረጃጀት መርሆዎች ይኑረን? ከምን ዓይነት አመለካከት የሚነሳ አደረጃጀት ይኑረን? ምን ዓይነት አሰራር መርሆዎች ይኑረን? . . . ወዘተ የሚሉ መሰረታዊ ነጥቦችና ጥያቄዎች የአመለካከት ጉዳይ የሚያስነሱ ናቸው። በመሆኑም በአደረጃጀት ጉዳይ ላይ የሚፈጠር ልዩነት መሰረታዊ የድርጅት ዓላማዎችና አቅጣጫዎችን የሚፃረር ትልቅ የልዩነት ነጥብ ሊሆን ይችላል። በአንዳንድ አብዮቶች ውስጥ የተራማጅና የአድህሮት መለያ ነጥብ ሆኖም ታይቷል፡፡

III. ከዚህ በመነሳት በአሁኑ ሰአት በአገራችን በኢህአዴግ ውስጥ እየተነሳ ያለው ከግንባር ወደ ውሁድ ፓርቲ የመሸጋገር ጉዳይ በመርህ ደረጃ መጠናት ያለበትና የጥናቱ ውጤት ቀርቦ ውይይት ማድረግ ተገቢ ቢሆንም፤ በደምሳሳው አንድ ውህድ አገር አቀፍ ፓርቲ አያስፈልግም ባንልም ከተጨባጭና ወቅታዊ የአገራችን ሁኔታ ውህደት ምን ማለት ነው? ከምን ይነሳል? በየትኛው እምነትና አመለካከት የሚመራ ውህደትና ለውህደት የሚያስፈልጉ እምነቶችና መለያዎች የትኞቹ ናቸው? በዚህ ረገድ ያሉ የአብዮቶች ተሞክሮ፣ የራሱ የኢህአዴግ ተሞክሮ በብቃት በንቃት መታየት አለባቸው። ይህ ብቻ ሳይሆን አደረጃጀቱ እንዴት መሆን አለበት? በየትኛው መርህ ነው የሚመራው? ምን ዓይነት ሕገ ደንብና አሰራሮች ይኖሩታል? ከየትኞቹ መርሆዎች ይነሳሉ የሚሉትን ጉዳዮች በማየት ሳይንስዊ ትጥቅ ታጥቀን አቋማችንን በመያዝ የሞት የሽረት ትግል ማካሄድ ይኖርብናል።

### 1.2. በፓርቲ ውህደት ሂደት የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚታዩበት አቅጣጫ

I. በዓለማችን ብዙ አብዮቶች ተካሂደዋል። የብርኸዋ አብዮት፣ የላብ አደር አብዮቶችና አመፆች፣ በተለያዩ ተራማጆች የተመሩ ዴሞክራሲያዊ አብዮቶች ወዘተ.. በአውሮፓ፣ በላቲን አሜሪካ፣ በኤስያና በአፍሪካ አገራት ፓርቲዎች በተናጠል፣ በግንባርና በውህደት መርተው ድልና ውድቀት አስተናግደዋል። እንደገና

ተስተካክለው የተነሱም አሽናፊ ሆነዋል። በዚህ የተለያየ የዓለማችን የአብዮቶች ውጣ ውረድ ውስጥ ባጠቃላይ  በተለይ ደግሞ በውህደት ወቅትም ሆነ በግንባር ምስረታ የታለፉባቸው ሂደቶች የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የውህደት ሂደቶችና የተጨመቁ ሃሣቦችንና በዳይሌክቲካዊ የስነ ሃሳብ የተቀመሩ ሃሳቦችን በአጭሩ ማየቱ አስፈላጊ ነው።

II. ውህደትም ሆነ ስትራቴጅካዊ ግንባር በተለይ ወደ አንድ ፓርቲ የሚደረግ የውህደት ጉዞ የላቀውና የመጨረሻው የመተማመንና የመግባባት ደረጃ ነው። በመሆኑም እዚህም እዝያም የነበረውን ማሰባሰብ፣ የመገጣጠም ወይም ማቀላቀል ሳይሆን የላቀ የአስተሳሰብና የአመለካከት ጥራት በማረጋገጥ እንዲሁም ይህንን ብቃት ባለው አደረጃጀት በማጀብ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የአመለካከትና የተግባር አንድነት በማረጋገጥ አዲስ ያልነበረ የለውጥ ዓቅም የሚመዘገብበት ነው። ለዚህ ሲባል ውህደቱ ወደ ላቀ የፕሮግራም፣ ስልትና ስትራቴጂ፣ ከዚህ የሚመነጩ ፖሊስዎችና የማስፈፀም ስትራቴጂዎች፣ እንዲሁም መተዳደርያ ደንቦችና ሌሎች አሰራሮችን ጠንካራ የአመለካከት የአንድነትና የተሟላ መግባባት መፍጠር ማለት ነው። ይህንን አንድ ታላቅ ምሁር (ቤንጃሚን ዲስራኤሊ የተባለ) አሁኑ በእንግሊዝ አገር ያለውን ዘመናዊ ኮንሰርቫቲቭ ፓርቲ በመመስረትና ፖሊስዎቹንና አጠቃላይ የቆመባቸውን አላማዎች በማስቀመጥ ረገድ ዋንኛ ተዋናይ የነበረ መሪና ፀሓፊ የፓርቲ ምንነትና አንድነትን አስመልክቶ እንዲህ ይገልፀዋል። "ፓርቲ ማለት የተደራጀና የተቀናጀ አመለካከትና አስተሳሰብ ነው" ይላል። ይህ አገላለፅ በአብዛኞዎቹ የፖለቲካ ሳይንቲስቶች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው። ሁሉም የአደረጃጀት ይዘትና መልክ ከዚህ የተወሃደና የተደራጀ አመለካከትና አስተሳሰብ እንደሚመነጭ ተቀባይነት ያለው ሃሳብ መሆኑን ማየት ይቻላል። ይህ ነው ለውህደት ወሳኙ እርምጃ።

III. በዚህም መሰረት በአብዮቶች ሂደት ለውህደት አራት መሰረታዊ ጉዳዮች እየበለፀጉ መጥተዋል፡፡ ከሁሉም በፊት የውህደት ወሳኝ እርምጃ የሚሆነው የሚያዋህድ ፕሮግራም፣ ስልትና ስትራቴጂ እንዲሁም ከዚህ በመነሳት ማዳበርና በተጨባጭ መዘጋጀት ነው፡፡ መሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ማስፈፀምያ ስትራቴጅዎችና ከዋና ዋናዎቹ  መለያ እምነቶች መቅረፅ፣ እንዲህ ያለ ይዘት ዝግጅት የሌለው ውህደት ገና ከጠዋቱ የተበተነ እንደሆነ እየታየ መጥቷል። ስለሆነም ውህደትም በተመለከተ ግልፅ የሆነ መስመር መቅረፅ የመጀመርያውና ዋነኛው እርምጃ መሆኑ ስነ- ሃሳባዊ ትንታኔ ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ አብዮቶችና እንቅስቃሴውን ከሚመሩ ፓርቲዎች ተጨባጭ ተሞክሮ እየተረጋገጠ የመጣ ነው።

IV. **ሁለተኛ፦** በውህደት ጉዳይ የታየው መሰረታዊ ነገር የሚዋሃዱት ወይም ስትራተጂካዊ ግንባር የሚፈጥሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ይዘትና ታሪካዊ አመጣጣቸውን እንዲሁም የሚያዋህዳቸውን ጉዳይ የሚገልፅ ህገ-ደንብና አሰራሮችን፣ እንዲሁም አደረጃጀት በግልፅ የማዘጋጀት አስፈላጊነት ነው። በብዙ ፖለቲካ ፓርቲዎች የመዋሃሃድ ሂደት የተረጋገጡ የፓርቲዎቹ ይዘት፣ ታሪካዊ አመጣጣቸው፣ በመካከላቸው የነበረ ትስስርና ልዩነት (መሰረታዊ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል) የሚንቀሳቀሱበት ነባራዊ ሁኔታ ወዘተ ... በጥልቀት ማጥናት፣ ማወቅና መገምገም፤ ውህደቱ እንዴት እንደሚፈፀም፣ እንዴት እንደሚፋጠንና ለዚህ

ሲባል ምን መደረግ እንዳለበት የሚያመላክት የጥናትና ግምገማ ማቴሪያል አስፈላጊ መሆኑ እየታየ መጥቷል። ከዚህ በዘለለ ሌላኛውና ከዚህ ጋር የሚተሳሰር መሰረታዊ ጉዳይ ዳግም ውህደቱን አቅፎ የሚይዝ የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት የሚፈጥር መተዳደርያ ህገ- ደንብና የተለያዩ አሰራሮችና፣ የአደረጃጀት መርሆች መቅረፅና ማዘጋጀት ሌላኛው የማይታለፍ ሂደት ሆኖ ታይቷል።

V. **ሶስተኛ:-** በነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ላይ የተመሰረተ ለውህደቱ የሚያመች ሰፊ የፖለቲካና የስነ- ሃሳብ መደላደል የመፍጠር እርምጃ ነው። የመወሃጃው መሰረታዊ ዓላማዎች ስልትና ስትራቴጂ መቅረፅንና ማጥራትን ጀምሮ ከታች እስከ ላይ በሚቀርቡ የፖለቲካና ስነ- ሃሳብ ጉዳዮች ከላይም ከታችም ለማረምና ለማጎልበት በአንድ በኩል፣ ለማስረፅ በሌላ በኩል ደግሞ ሰፊ የሆነ የተግባር እንቅስቃሴ የማድረግ አስፈላጊነት ሌላኛው አስፈላጊ እርምጃ መሆኑ ታይቷል። በአንድ በኩል በውህደቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ የሆነውን ህዝብ በጉዞው ውስጥ ለማሰለፍ፣ በሌላ በኩል ደግም የውህደቱ የምስረታ ጉዞ በትክክለኛው መንገድ እንዲጓዝ ለማድረግ ጠለቅ ባለ የፕሮፖጋንዳና በአጠቃላይ የማነቃቃት ስራ የታጀበ የስነ- ሃሳብ የፖለቲካ መደላደል የማንጠፍ ሂደት ከታች እስከ ላይ የነቃ ተሳትፎ መፍጠር በውህደት ሂደት ሆነ በስትራቴጂያዊ ግንባር ምስረታ ሌላኛው ቁልፍ እርምጃ መሆኑ ታይቷል።

VI. **አራተኛ:-** ከሶስተኛው ነጥብ ጋር የተሳሰረ ሆኖ፣ ግን ደግሞ ለውህደት የሚደረገው ሰፊ እንቅስቃሴ የራሱ የውህደቱን ኮር አመራርና ሌሎች አመራሮች የመፍጠር፣ የማሰባሰብና የመገንባት አስፈላጊነትም ሌላኛው እርምጃ ሆኖ መጥቷል። የውህደቱ ሂደት፣ ሄዶ ሄዶ በመሰረታዊ የመወሃጃ አቅጣጫዎች፣ መርሆዎችና አስተማማኝ የአመለካከትና የተግባር ጥራት ያረጋገጡ መሪዎች ስብስብ እንደሆነ፣ ስለዚህም ከማህበራዊ መሰረቱ በመስመርና በህዝብ ወገንተኘነቱ፣ ህዝብን በመምራት ብቃትና አቅም እየተለየ ውህደቱ የላቀ ብቃትና አብዮታዊነት በተላበሰ መሪና አመራር የሚታነፅበት ሂደት መሆኑ፤ በዚህም በቅድመና በድህረ ውህደት ደረጃዎች ማህበራዊ መሰረቱን ባላሰለሰ ትግል በአስተማማኝነትና በፅናት ለማሰለፍና በመጨረሻም ጥራት ያለው ጉባኤ ተካሄዶ ውህደት መፈፀምን ነው ያስተማረው። ከዚህ በመነሳት በኢህወዴግ ውስጥ እየተነሳ ያለው የውህደት ጥያቄ በዚህ ዓለም አቀፋዊ እይታ (Perspective) እና ተሞክሮዎች በብቃት መታየት ያለበት ጉዳይ ነው።

### 1.3. በስትራተጂካዊ ግንባር ምስረታና በደኢህዴን ውህደት የኢህአደግ ተሞክሮ

1. በኢህአዴግ እየተነሳ ያለው የመዋሃድ ወይም ደግሞ አንድ ወጥ የሆነ አገር አቀፍ ፓርቲ የማድረግ ጥያቄ አጠቃላይ እይታው ምን መሆን እንዳለበት ለማስቀመጥ ተሞክሯል። ይህ እንዳለ ሆኖ ኢህአዴግ በአደረጃጀት አንድ ፓርቲ ያልነበረ ቢሆንም በፕሮግራም በስልትና በእስትራቴጂ እንዲሁም ከዚህ የሚመነጩ መሰረታዊ የሆነ ፖሊሲዎችና ማስፈፀሚያ እስትራቴጂዎቻቸው እንዲሁም መተዳደርያ ህገ- ደንቡን በግልፅ በማስቀመጥ ስትራተጂካዊ ግንባር ሆኖ ቆይቷል። በኢህአዴግ ውስጥ ደኢህዴን ከተለያዩ የብሄሮችና ብሄረሰቦች ድርጅቶች ወደ አንድ ድርጅት የመጣበትን አሰራር በማየት ተጨማሪ ትምህርትና

ግንዛቤ መፍጠር የተሻለ ነው። በዚህም መሰረት ህወሓት፣ ኢህዴንና ኦህዴድ እንዲሁም ደኢህዴን በጋራ ወደ ኢህአዴግ ምስረታ የተሸጋገሩበት የህብረት ሂደት እንዲሁም የደኢህዴን ህብረትና ጥምረት ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል።

II. ለኢህአደግ ምስረታ የህወሓትና ኢህዴን የህብረት ሂደት በሁለቱም ድርጅቶች በዓላማ ዙርያ የአመለካከት አንድነት፣ ስልትና ስትራቴጂ ለመፍጠር የሚያስችል ረጅም ግዜ የወሰደ ተከታታይና በሳል ውይይት ተደርጓል። እነዚህ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ አብዮት እንደሚካሂዱና አራት አላማዎች እንደሚያሳኩ የጋራ አመለካከት ለመያዝ ከ1973 ዓ/ም ኢህዴን ጉባኤ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ኢህአዴግ ምስረታ 1981 ዓ/ም ድረስ ተከታታይ ውይይት፣ ጥናትና ግምገማ በማድረግ ልዩነቶቻቸውን በማጥበብ፣ ያልተመለሱ ጥያቄዎችን በየደረጃው በመመለስና አዳዲስ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ማስተካከያ በማድረግ በአላማ ላይ የተመረኮዘ የጋራ አመለካከት መፍጠር ችለዋል። እነዚህ አራት አላማዎች ደግሞ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን፣ ፊውዳሊዝምንና የውጭ ጣልቃ ገብነትን በማስወገድ እና በመመከት፣ የብሄር ብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ማስከበር በሚሉ አንኳር ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ ብሄሮች የሉም፣ ትግሉ ለአንድነት ብቻ ይሁን፣ የኤርትራ ጥያቄም የብሄር ጥያቄ እንጂ የቅኝ ግዛት ጥያቄ አይደለም ወዘተ ... የሚሉ የልዩነት የክርክር ነጥቦች ሆነው በሰፋፊ ውይይትና ክርክር እየጠበቡ በመምጣታቸው ሁኔታው ለኢህአዴግ ምስረታ እየተመቻቸ መጥቷል።

III. በስትራቴጅና ስልትም ደረጃ ጠላትና ወዳጅን መለየት፣ የወዳጅ ሃይሎችን የእያንዳንዳቸውን አስተዋፅኦ መለየትና እነርሱ የሚሰማሩበትንና፣ የሚታነፁበትን አቅጣጫ መለየት እንደዚሁም የድርጅቶች ህብረት በተለይ ስትራቴጂካዊ አጋርነት በሚፈጥሩ ሃይሎች መካከል የሚመሰረት ግንባርን በሚመለከት ረጃጅምና ሰፋፊ የሆኑ ውይይቶች ተደርገው ኢህዴን፣ ኦህዴድና ህወሓት ህብረት ፈጥረው ኢህአዴግ ሲመሰርቱ ጠላትና ወዳጅን ለይተው፤ የእያንዳንዱ ወዳጅ ሃይል ሚና ምን እንደሆነ ለይተው በትግሉ እስትራቴጂ ላይ የአመለካከት አንድነት በመፍጠር ነበር ኢህአዴግን የመሰረቱት፡፡ በስልትም ዙርያ ቢሆን ኢህአዴግም ሆነ የአባል እህት ድርጅቶች የትግል አግባብ ብሄራዊና ህብረ ብሄራዊ አደረጃጀትና በተራዘመ የገጠር ትጥቅ ትግል ለድል መብቃት መሆኑን በመድረኮች በተካሄደ ትግል ስምምነት ላይ በመድረስ ነው የኢህኣዴግ ምስረታ የተበሰረው።

IV. በአዲሱና እያደገ በመጣው የዓለማችን ሁናቴም በተመሳሳይ ከ1982-1983 ዓ/ም የሁለት ልዕለ ሃያላን ካምፕ ፈርሶ አሜሪካ ብቸኛዋ ልዕለ ሃያል ሆና ከወጣች በኋላ የተፈጠረውን አጠቃላይ ሁኔታና የአሰላለፍ መዛባት እንዲሁም የአገር ውስጥ አሰላለፍን በጥልቀት በመገምገም የነፃ ገበያና የህብረ ብሄራዊ የፖለቲካ ስርዓት ግንባታ እንዴት መካሄድ እንዳለበት በተከታታይ ጥናቶች፣ ውይይቶች ክርክሮች በማካሄድ ስምምነት ላይ ተደርሶ ከአገሪቷና አጠቃላይ ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ጋር የሚስማማ የፕሮግራም ማስተካከያ ተደርጎ ነበር መስራች ጉባኤ በማካሄድ ኢህአዴግ የተመሰረተው፡፡ በዚህ አገባብ በመሰረታዊ የመስመር ጥያቄ ላይ በቂ ጥናት ውይይትና ክርክር ከተካሄደና የመስመር አንድነት ከተፈጠረ በኋላ ነበር

ሁሉም ወደ አንድነት የመጡት። ኢህአዴግ በዚህ ጥራት ያለው ሂደት የተፈጠረ ስለሆነ ነው ብዙ ተግዳሮቶችን እየተሻገረ መጓዝ የቻለው።

V. የደኢህዴግና የዴኢህዴን ግንባርና ስምረትም በተመሳሳይ ሂደት ነበር የተካሄደው፡፡ ደርግ ከተገረሰሰ በኋላ መጀመርያ 16 ድርጅቶች ነበር የተመሰረቱት፡፡ የዛን ግዜ ይህ አደረጃጀት የሚፈጥረው የፖለቲካዊ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መናጋት በተመለከተ በራሳቸው ሙሁራንና የአገር ሽማግሌዎች እየተነሳ ውይይት እየተደረገበት ከቆየ በኋላ ኢህአዴግ ከድርጅቶቹና ሽማግሌዎቹ ጋር በመሆን 16ቱ ድርጅቶች አንድ ግንባር እንዲፈጥር ህብረት እንዲመሰርቱ በየድርጅታቸው እስከ ህዝቡ የጋራና የተናጠል መድረኮችን በማዘጋጀት ተደጋጋሚ ክርክር ተደርጎ በጠባብና በዴሞክራሲያዊ ብሄርተኝነት መካከል የነበረው የአመለካከት ልዩነት ከተለያዩ አካላት ጋር በተደረገው ሰፊና ተከታታይ ውይይት ከኢህአዴግ ተሞክሮ ጋር እየተዛመዱ በመጨረሻ የጋራ አመለካከት ተፈጥሮ ነው በጉባኤ ፀድቆ ግንባሩ የተፈጠረው ፡፡ ይህ ግንባር እንደ አንድ የኢህአዴግ አካል ሆኖ ሲታገል ቆይቷል። ከዛም ተከትሎ የተለያዩ ክልሎችን መስርተው የነበሩ ብሄረሰቦችም ወደ አንድ ክልል ቢሰባሰቡ የበለጠ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ትስስርና አንድነት ቢፈጥሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ታምኖበት በጉባኤ አንድ ውህድ ደኢህዴን ተመስርቷል።

VI. በአጠቃላይ መስመር፣ የአደረጃጀት አቅጣጫና የመተዳደርያ ህገ-ደንብ በቅድምያ በማንጠር በነርሱ ላይ የጋራ የአመለካከትና የተግባር አንድነት በመፍጠር መራመድ ለአስተማማኝና መርህ ላይ ለተመሰረተ ህብረት /ግንባር/ በተለይ ደግሞ ለውህደት ያለው ፋይዳ መተኪያ የለውም። የዓለማችንና የአገራችን ድርጅቶች ተሞክሮ የሚያስተምረን ግልፅ ባልሆነና የጋራ አመለካከት መፈጠሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ በግዝያዊ ዓላማ ተመስርቶ የሚፈጠር ግንባርም ሆነ ውህደት ዕድሜ የሌለው ፈራሽ መሆኑን ነው፡፡ በአውሮፓ፣ በጣልያን፣ በእንግሊዝና በፈረንሳይም ፓርቲዎች በተደጋጋሚ ህብረት ፈጥረው በተደጋጋሚ ሲፈርሱ በየግዜው የጥምር መንግስት መሰርተውም ቢሆን ሲፈርሱ ማየት የተለመደ ነው። በአገራችንም እንዲሁ በየግዜው በውስጥም ሆነ በውጭ ለምርጫ ተብሎም ኢህአዴግን ለመቃወም ሲመሰረቱ የነበሩ የድርጅቶች "ህብረት"፣ ውህደት፣ ዕድሜ አልነበራቸውም። ከምርጫ በኋላ ብዙዎቹ ይፈርሱ ነበር። የኢህአዴግም ሆነ ደኢህዴን ምስረታ ግን አስቀድሞ ህብረት የምንፈጥርበት አልያም የምንዋሃድበት ጉዳይ ላይ ውይይትና ክርክር በማካሄድ የጋራ አመለካከት መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ የአደረጃጀት አቅጣጫና መተዳደርያ ህጉ የሚስማማ ከሆነ በኋላ ስለተመሰረቱ ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል። አንፃባራቂ ድሎችም በጋራ እያስመዘገቡ ይገኛሉ። ከዚህ በመነሳት አሁንም በመስመር፣ በአደረጃጀት አቅጣጫ ህገ- ደንብ አንድ መሆናችን ሳይረጋገጥ ውህደት መፍጠር ግን ዕድሜ የሌለውና መርህ አልባ ውህደት ይሆናል።

### 1.4. ለውህደት ይቅርና ላለበት ግንባርም የማይበቃ ኢህአዴግ

1. /ህወሓት/ ኢህአዴግ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያክል ከባድ መስዋእትነት ከፍሎ የታገለለትና የድሉ ዋነኛ ሚስጥር የሆነው ፕሮግራም ራእይና ተልእኮው አሁን ከኢህአዴግ ጋር የለም። ከዚህ የሚመነጩ መሰረታዊ ፖሊሲዎችና የማስፈፀምያ ስትራቴጂዎቹ አደጋ ተጋርጦባቸዋል። የአብዮታዊ ዴሞክራሲ

አስተሳሰብ (ልማታዊ ዴሞክራሲ) የኢህአዴግ መመርያ መሆኑ ተቋርጧል ማለት ይቻላል። ይህ አስተሳሰብ ጊዜው ያለፈበት አስተሳሰብ እንደሆነ ተደርጎ ተደምድሟል። በአሁኑ ሰአት በኢህወዴግ ውስጥ "መንገዳችን የሊበራል ዴሞክራሲ ነው" ብሎ ለማወጅ ምቹ ሁኔታ እየተጠበቀ ይገኛል እንጂ ሁሉም ነገር አብቁቶለታል። በኢትዮጵያ ሊበራል ዴሞክራሲ የሚባል ሽፋን እንጂ የጥገኝነት አማራጭ ወይም ደግሞ ኪራይ ሰብሳቢነት ነው። በመሆኑም በነባራዊነቱ የኢህአዴግ ፕሮግራም በተግባርና በአስተሳሰብ የጥገኝነት ፕሮግራም ሆኗል።

II. ከተጨባጭ ፕሮግራሙ የሚመነጩት የኢህአዴግ ስልትና ስትራቴጅዎችም ፈርሰዋል። በአጠቃላይ የኢህወዴግ የመደብ ትንተና እይታ ግዜው ያለፈበት የኮሚኒስት አስተሳሰብ ተደርጎ ተደምድሟል። በአሁኑ ሰአት ወዳጅ፣ ጠላትና መሃል ሰፋሪ የሚባል የትግል ትንተና እየጠፋ ነው። ምንም የአሰላለፍ ትግል ወደ ሌለበት የእድር ማህበር ወደ መሆን እየተሸጋገረ ይገኛል። መሰረታዊና መለስተኛ የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ቅራኔዎች የሚባል ትንተና የለም፡፡ ኢህአዴግ አጠቃላይ የህብረተሰብ ህጎችን በተለይ ደግሞ ተጨባጭ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ሁኔታ መሰረት አድርጎ የነዚህን የህብረተሰብ ሃይሎች የጥቅምና የቅራኔ ልዩነት ተንትኖ የኢትዮጵያ ማህበረሰብን እድገት ወደፊት የሚያስፈነጥር ውሳኔ የሚወስን የወቅቱ ሞተር ሆኖ የሚያንቀሳቅሰው በአብዮታዊ ዴሞክራሲና በኪራይ ሰብሳቢ ጥገኝነት መካከል መካሄድ የነበረበት የመደብ ትግል እየሞተ በመሆኑ ህብረተሰብን የሚያንቀሳቅስ ሞተር መሆኑን እያቋረጠ ይገኛል። ሕብረተሰብን ከአዙሪት የሚያወጣው የመደብ ትግል እየጠፋ ይገኛል፡፡ ይህ ዋነኛ የኢህአዴግ መለያና ለውህደት ቅድመ ሁኔታ የሆነው ጉዳይ ጀምበር ጠልቃበታለች።

III. የኢህአዴግ መተዳደርያ ህገ-ደንብ፤ አሰራሮችንና አደረጃጀቶች እራሱን የሚገሩ መሆናቸው እያቋረጡ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ሁሉም የድርጅቱ ህጎችና አሰራሮችን የይስሙላ ናቸው። ከህወሓት ውጭ የኢህአዴግን ህገ-ደንብና አሰራሮች የሚያከብር የለም። የአመለካከትና የተግባር አንድነትን ገርቶ አቅፎ የሚይዝ ህገ-ደንብ የለም፡፡ የኢህአዴግ ድርጅቶች በየአቅጣጫው ተበትነዋል። የኢህአዴግ ድርጅቶች ከድርጅቱ ህገ- ደንብ ውጭ ከተለያዩ ጥገኛ ድርጅቶች ጋር ጥምረትም ውህደትም እየፈጠሩ ይገኛሉ። ቡድንተኝነትና በመርህ ላይ ያልተመሰረተ ትስስር በሰፊው ተፈጥሯል። በጠላትነት የሚተያዩ ድርጅቶች ሆነዋል። የጋራ አመለካከትና ተግባርም የለም፡፡ ገዢ የሆነ ህገ- ደንብ የላቸውም። በመሆኑም ለውህደት ይቅርና አሁን ያሉበትን ግንባር የሚያቀናጀው ህገ- ደንብ በተጨባጭ ፈርሷል።

IV. ከገባበት ጥገኛ መበስበስ ያልወጣ ድርጅት:- በተደጋጋሚ እንደተገመገመውና እንደታየው በራሱ በውስጣዊ ችግር በጥገኛ መበስበስ አዝቅት ውስጥ ከገባ ዓመታት አስቆጥሯል። ይህ የጥገኛ መበስበስ በሦስትና አራት መሰረታዊ ችግሮች የሚገለፅ ነው። አንደኛ፣ በኢህአዴግ ውስጥ ከላይ እስከ ታች በሁሉም መሰረታዊ ጉዳዮች የጠራ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አለመያዝ፤ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከቶች ከጥገኛ አመለካከቶች ጋር እየተዳቀሉ ሰፊ የሆነ የአሰላለፍ ጎራ መደበላለቅ አንደኛው የመበስበስ ገፅታና ምንጭ ነው። በድርጅታችን በማህበረሰባችን ውስጥ የፀረ- ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ተግባር እየጎለበተ፤

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ትግል እየተቀዛቀዘ መምጣቱ ሁለተኛው ምንጭ ነው። ግለኝነት እየሰፋ፣ አድርባይነትና መቻቻል እየተጠናከረ፣ ሙስናን እየወለደና እያጠናከረ መምጣቱም ሶስተኛው ምንጭ ነው። እነዚህ ባሉበት ሁሉ ጥገኝነትና የሱ መገለጫ የሆኑት ትምክህት፣ ጠባብነትና ህዝበኝነት ጫፍ የወጡበት፤ በዚህም ምክንያት ስልጣን በጥገኛ መንገድ በመያዝ የተገለፀው ጥገኛ የመበስበስ ኢህአዴግ ውስጥ በነበረበት ይገኛል ብቻ ሳይሆን የጥገኛ መበስበስ ኃይል ስልጣን ይዟል።

V. በመሆኑም ኢህአዴግ በአሁኑ ሰአት ከገባበት የጥገኛ መበስበስ አዘቅት መውጣት አቅቶት በካባድ የስነ- ሃሳብ ቀውስ ውስጥ ገብቶ፣ በከፋ የፀረ- ዴሞክራሲና የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭነት አዙሪት ውስጥ የገባበት፤ ሙስና ከማናቸውም ግዜ በላይ የነገሰበት፣ ጉቦና ሌብነት ስርዓት የሆነበት፣ የኪራይ ሰብሳቢነት መረብ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የተጠናከረበት፣ አፋኝ የሆኑ የመንግስት መዋቅሮች የመንግስትን ትእዛዝ ለመፈፀም በሚያስችል መልኩ የሚዋቀሩበት፣ በስልጣን ላይ ያለው ጥገኛና አለም አቀፍ መተሳሰር በመፍጠር ጎልብቶ የአገር ሉኡላዊነት ተደፍሮ ከማናቸውም ግዜ በላይ ትምክህት፣ ጠባብነትና ብሄርተኝነት ገንግነው፣ የትምክህት ኃይል የወደቀውን አሃዳዊ ስርዓት ለመመለስና ባንፃሩም የፌዴራል ስርዓቱን ህገ- መንግስቱን ለማፍረስ በሙሉ ዓቅም የሚረባረብበት የዚህም ዋነኛ መሳርያ ኢህአዴግን በመወከል በስልጣን ላይ የሚገኘው ሃይል የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም ብሄራዊ ማንነትና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት አደጋ ውስጥ ስለወደቀ ጭቁን ብሄሮች በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት አማራጭ ላይ ተስፋ የቆረጡበት፣ ብሄራዊ ጭቆናን ለመመለስ ያለሃፍረት በይፋ የሚለፈፍበት፣ የሁሉም ችግሮች ምንጭ የብሄር ፖለቲካ በዚህ አገር ተግባራዊ መደረጉ ነው ተብሎ የሚነገርበት ወቅት ላይ ተደርሷል። በአጠቃላይ አሁን ኢህአዴግንና በርሱ የሚመራውን ልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት በመምራት ላይ ያለው ኢህአዴግና የገዥ መደብ ቡድን መለያው ፀረ- አብዮት፣ ፀረ- ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ሙስናና ብልሹ አሰራር ገዥ የሆነበት በውጤቱም አገር በመበታተን ጫፍ ላይ የደረሰበት ወቅት ላይ የሚቀነቀን "ውህደት" የሚባል ተረት ተረት ሊታለም አይችልም፡፡

### 1.5. ታድያ የአንድ አገር አቀፍ ውሁድ ፓርቲ ጥያቄ እንዴት ይሁን?

i. አንድ ወጥ የሆነ አገር አቀፍ ውሁድ ፓርቲ ለመመስረትና ኢህአዴግን ከግንባር ወደ ውሁድ ፓርቲ ለማሸጋገር ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ሊታገል የሚፈልግ ይህንን ጥያቄ በማንሳት ኢህአዴግን ወደ ውህደት ለማሸጋገር በየትኛውና በምን መንገድ ታግሎ ሊያስተካክል እንደሚችል የሚያይበት፤ ኢህአዴግን የሚያድንበት ወጣም ወረደ የፓርቲ ውህደት ጥያቄ ጉዳይ ምን ይሁን? አራትና አምስት መሰረታዊ ነጥቦች በማንሳት መሆን ያለበትን እናስቀምጥ፡፡ ከሁሉም በላይ ኢህአዴግ አሁን የገጠመው ችግር የአስተሳሰብ ነው ወይስ የአደረጃጀት ችግር? ያለ ጥርጥር የኢህአዴግ ችግር የአደረጃጀት ሳይሆን የአስተሳሰብ የጥገኛ መበስበስ ችግር ነው፡፡ ይህንን ችግር ሳይሻገሩ ከአለም ቀዳሚ የሚባለው አደረጃጀት ቢፈጠርም የሚመጣ ለውጥ አይኖርም፡፡ ስለዚ ኢህአዴግ **መጀመርያ** ያመመውን ቦታ መታከም አለበት፡፡

ሀ/ የኢህአዴግ ዋነኛ ችግር የአመለካከት ችግር መሆኑን ራሱ የውሁድ ፓርቲ አስፈላጊነትን ለማጥናት የተሰማራው የጥናት ቡድን "የጥናት ግኝት" ብሎ ባቀረበው ውጤትም የኢህአዴግ አልፋና ኦሜጋ ችግሩ የአመለካከት ችግር ጥልቅ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ ከተቀመጡ የተወሰኑትን ለማንሳት ያክል በስፋት የተገለፀው ፀረ-ዲሞክራሲ መኖር ነው፡፡

የማእከላዊነት አለመኖር፣ የጋራ ውሳኔዎች አለመፈፀም፣ በእህት ድርጅቶች መካከል ከባድ የመጠራጠር ሁኔታ መኖር፣ የፅንፈኛ ብሄርተኝነት መካረር፣ ለሙስና ሰፊና የተመቻቸ ሁኔታ መኖር፣ የውስጠ ድርጅት ዲሞክራሲ ቅጥ ያጣ መሆን፣ በድርጅቱ ውስጥ መርህ አልባ ግንኙነት መኖር፣ የፓለቲካ ስራዎች መዳከም፣ የኢህአዴግ አባላት በድርጅታቸው ላይ እምነት ማጣታቸው፣ ነፃ የሃሳብ ክርክር አለመኖር፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ችግርና የተለየ ሃሳብ አለመቀበል፣ ማሸማቀቅ፣ ስም ማጥፋት ማስፈራራት፣ የሃሳብ ድርቀትና ከመስመር የመውጣት አዝማማያ መኖርን ወዘተ... ያስቀምጣል፡፡

ለ/ በመደብ ትግል ላይ ዓበይት ችግሮች እንዳሉ አድርባይነትና፣ መቻቻል፣ ከአካባቢህ ልጅና ጓደኛህ ጋር በትውውቅ ትስስር መኖር፣ የጥቅም ትስስር መኖር፤ መተጋገዝ፣ መደማመጥና መተማመን እንደተሸረሸረ፣ ብሄራዊ ድርጅቶች ለጋራ ዓላማ የተሰለፉ መሆናቸው ቀርቶ እርስ በርሳቸውን እንደ ተፎካካሪ ፓርቲዎች የሚካሰሱበት የአንድ ግንባር አባላት የማይመስሉበት፣ እርስ በርስ የሚጠላለፉ፣ የሚናቆሩና በአሳፋሪ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ነው የተገለፀው፡፡ እንደዚሁም አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር እንዳልተቻለ፣ የፍትሓዊነት ተጠቃሚነት ችግር እንዳለ፣ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ደግሞ ይህንን ማህበረሰብ የሚያዳክም የከረረ ብሄርተኝነት እያደገ መምጣቱ፣ በየድርጅቱ ያፈነገጠ አካሄድ መኖር፣ የአገር አንድነትና ህብረ ብሄራዊነት እንደተዳከመና አውራ ፓርቲ መሆን ችግሮች እንዳሉበት አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ በመፍጠር ረገድም ችግር እንዳለ. . . . ወዘተ ተነስቷል፡፡

ሐ/ ምክረ ሃሳብ በሚል የተቀመጡት ነጥቦች ደግሞ፣ እነዚህን ችግሮች በነባሩ አደረጃጀት የማስተካከል ዕድል ጠባብ እንደሆነ፣ በመሆኑም አደረጃጀቱ ሊስተካከል እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም አደረጃጀቱን በማስተካከል የተለጠጠ ብሄራዊ ማንነትን ማስተካከል እንድሚያስፈልግ፣ በዚህ ረገድ በብሄራዊ ማንነት ግንባታ ረገድ በከፍተኛ ሁኔታ ተሰርቶበታል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በአገራዊና በኢትዮጵያዊ ማንነት ስላልተሰራበት አደረጃጀቱ ይለወጥ፣ ካሁን በኋላ የኢትያጵያውነት ማንነት ግንባታ በደንብ ይሰራ፣ ህገ-መንግስቱ ለአንድ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ፣ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ከሰጠው እውቅና ጋር የኢህአዴግ አደረጃጀት ስላልተጣጣመ ይሰተካከል፣ በማንነት ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ አደረጃጀትና አስተሳሰብ አያዋጣም? ለእኩልነት፣ ለአንድነትና ወንድማማችነት የሚመች አይደለም፤ የህዝብን እኩልነት የሚረጋገጠው በህገ-መንግስት እንጂ በፖለቲካ ፓርቲዎች አይደለም፣ የኢህአዴግ አባላት በታችኛው እርከን ላይ ስላልታደሱ ይታደሱ፣ የዓላማ ፅናት የለም፤ ግላዊ ጥቅመኝነት ነው እያስቀደመ ያለው፡፡

የአመራር ግንባታ የለም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ምክረ-ሃሳብ ሲጠቃለል ኢህአዴግ አደረጃጀት አንድ ፓርቲ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡

**መ**/ የጥናት ግኝነት ተብሎ የተገለፀው በኢህአዴግ ውስጥ ከባድ የአስተሳሰብ ችግር እንዳለ፣ እንዲያውም ዋንኞቹ የጥገኛ መበስበስ ምልክቶች፣ ፀረ-ዲሞክራሲ፣ ሙስና፣ የግንባታ የፖለቲካ ብቃትና የመስመር ቁርጠኝነት ችግር መኖር በውጤቱም የከረረ ብሄርተኝነት እየገነነ መምጣቱ፣ በማንነት ላይ የተመሰረተ ፖለቲካና አደረጃጀት እንደማያስፈልግ፣ ከወገብ በታች ተሃድሶ እንደማያስፈልግ፤ ተጠቅሶ ዋንኛ መፍትሄውም አንድ ውሁድ ፓርቲ መሆን አለበት በሚል ምክረ ሃሳቡ ያጠቃለላል፡፡ ይህ ጥናት በራሱ በጣም መሰረታዊ መዛባት ያለበት ነው፡፡ ከመጀመርያው በቅኝት የሄደ ሆኖ እንደአቅሚቲ በግኝቱ መሰረት እንኳን ቢሆን መሰረታዊ የሆነ የአስተሳሰብና የአመለካከት ችግር እንዳለበት የሚያመላከት ነው፡፡ ይህ የጥናት ውጤት መሰረታዊ የሆኑ የአመለካከት ችግሮች በአደረጃጀት ይፈታሉ ነው እያለን ያለው፡፡

የችግሩ ዋነኛ ምንጭ አደረጃጀት አይደለም፡፡ የመፍትሄው ቁልፍም አደረጃጀትን መቀየር አይደለም፡፡ ችግሩ የጥገኛ መበስበስ ብልሽት ነው፡፡ መፍትሔው ደግሞ ጥገኛ መበስበስን ሊያስወግድ የሚችል የመደብ ትግል ማቀጣጠል ነው፡፡ ዋነኛው የጥገኛ የገዢ መደብ መበስበስ ነው፣ ዋነኛው መታደስ ያለበትም ያልታደሰው ከፍተኛው አመራር ነው፡፡ ዋነኛው አደጋ የታችኛው መዋቅር አይደለም፡፡ በዚሁም መሰረት የኢህአዴግ የአንድ ፓርቲ ውህደት ጥያቄ የአደረጃጀት ሳይሆን ቅድሚያ የአስተሳሰብ ነው መሆን ያለበት፡፡ የከፍተኛው አመራር ተሃድሶ ነው መከናወን ያለበት፡፡ ይህንን መረዳትም ለአንድ ፓርቲ ምስረታ የመጀመሪያ እርምጃው ይሆናል ማለት ነው፡፡

ii/ ለአንድ ፓርቲ ምስረታና ለውህደት **ሁለተኛ** ወሳኙ ቅድመ ሁኔታ የሚያዋህደንን እንለይ የሚለው ነው፡፡ ከአጠቃላይ የውህደት እይታዎችና (Perspective፡ የአለማችን አብዮተኞችና ፓርቲዎች፣ የኢህአዴግ ተሞክሮ አንደሚያመላክተው፣ ለውህደት የመጀመርያ እርምጃ የሚያዋህድህን መለየትና በዙርያው ትግል ማድረግ ነው፡፡ ኢህአዴግና አባል ድርጅቶቹ፣ አንድ መስመር፣ አንድ ስትራቴጂና ስልት አንድ ህገ-ደንብ ይዘው ነበር ሲታገሉ የቆዩት፡፡ በዚህ የወሰድነው እንደሆነ ኢህአዴግ አደረጃጀቱ ነው ብሄራዊ መልክ የነበረው እንጂ አንድ ድርጅት ነው፡፡ ኢህአዴግ ከነ ጉድለቱም በተሃድሶ ሙሉ በሙሉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ባህሪውን የጠበቀ ቢሆን ኖሮ የውህደታችን መሰረት ምን እንደሆነ መገመት ይቻል ነበር፡፡ አሁን ግን፡-

ሀ/ በሁሉም የድርጅት የፕሮግራም ጥያቄዎች፣ ስልትና እስትራቴጂ፣ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ሙብትና ብሄር ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም ወዘተ...የመሳሰሉ መለያ እምነቶች ላይ ድርጅቱን እየመራ የሚገኘው በከፍተኛው የድርጅቱ አመራር እርከንና በአባል ድርጅቶች መካከል መሰረታዊ ልዩነት ተፈጥሯል፡፡ ኢህአዴግ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በዚህ ፅሑፍ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት ልንወሃድ ከሆነ የምንገነባው ስርዓት ምንነት፣ ዋነኞቹ ችግሮችና መፍትሄዎቹ፣ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ

ፖሊስዎችና እስትራተጂዎች፣ በ27 ዓመታት ውስጥ የተመዘገቡ ድሎችና ምንጫቸው፣ በፖሊሲ ነፃነትና የአገር ሉአላዊነት፣ በማንነት ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝምና የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብቶች…ወዘተ በሚሉ መሰረተዊ ጉዳዮች ሲታይ በሚያዋህድ ደረጃ ላይ አንገኝም፡፡ በመሆኑም አንድ የሚያደርግ የጋራ አመለካከት በሌለበት ወቅት ድርጅት መጠን እንደ ድርጅት ህልውና ሊኖረው አይችልም፡፡

ለ/ አንድ የሚያደርግ መስመርና አመለካከት በሌለበት መቢደን፣ የድርጅት መበታተንን ማስከተሉ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ከውህደት አስቀድሞ እንድንዋሃድ የሚያደርግ ግልፅና ፅኑ የሆነ መስመር መያዝ አለብን፡፡ ብሩህነት ላይ የተመሰረተ የጋራ አመለካከት፣ ለውዥንብር የማይጋብዝ በማያዳግም ግልፅ የሆነ የጋራ የአመለካከትና የተግባር አንድነት በፍፁም ሊታለፍ የማይገባው ጉዳይ ነው፡፡ ኢህአዴግን እየበታተኑ የሚገኙ ደባል አስተሳሰቦችን የሚለይ ድንበር፣ በግልፅ በማካለል፣ ብግልፅና በፅናት አስቀምጠህ ከዚህ ወደዚህ ብለህ በመለየት ነው ስለ ውህደት መነጋገር የሚቻለው፡፡ በፅኑ መሰረት ላይ የተገነባ ውሁድ ፓርቲ እንዲኖረን ከተፈለገ አሁን ላይ ያለው መዛባትና መደናገር አስቀድመን ማጥራትና ማስወገድ አለብን፡፡ መደናገርን በግልፅነት በመተካት እንጂ፣ ይህንን ሳያደርጉ የሚፈፀም ውህደት የለም፡፡

iii/ **ሦስተኛ፡-** ከውህደት አስቀድሞ ሊወሰድ የሚገባው እርምጃ ኢህአዴግን ማደስና አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ በአስተማማኝ የጥራቱ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡ ሁሉንም የዚህን ስርዓት ጉዞ የሚመራው ዋነኛ ሞተር ኢህአዴግ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ህብረተሰብ የሚንቀሳቀሰውን የመደብ ትግል የሚመራው ኢህአዴግ ነው፡፡ ሆኖም ግን አሁን ባለበት ቁመናና ገብቶበት ከሚገኘው የጥገኛ መበስበስ አዘቅት ሳይፈታ አንድ ውሁድ ፓርቲ የሚባል ነገር የለም፡፡ የአንድ ውሁድ ፓርቲን በተመለከተ እኛን ትርጉም የሚሰጠን የትኛውም አይነት ውህደት ወይም ጥምረት ሳይሆን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መስመር እምነቶቹ ላይ ሙሉ በሙሉ ተመስርቶ በሚፈጠር ስነ-ሃሳባዊ አንድነት፣ በርሱም አማካኝነት የሚመጣው የተግባር አንድነት ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ኢህአዴግ ጀምሮት ከሸፎበት የቀረውን ተሃድሶ እንደገና አንቀሳቅሶ በቁርጠኝነት ራሱን ለማደስ ትኩረት ሰጥቶ ከሰራበትና አንደገና ከተወለደ በኋላ ብቻ ነው የአንድ ውሁድ ፓርቲ አጀንዳ ሊነሳ የሚችለው፡፡

iv/ **አራተኛ፡-** ቀድሞ መስራት ያለበትና መግባባት ላይ ሊደረስበት የሚገባው ጉዳይ፣ ውህደቱ የሚተዳደርበት ህገ-ደንብ፣ ተግባራዊ የሚሆንበት አደረጃጀት፣ መርሆዎችና አስራሮቹን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ፅሑፍ ተደጋግሞ እንደተነሳው ውህደት የመጨረሻው የመተማመን ደረጃ ነው፡፡ ወሳኙ መተማመን ደግሞ በዓላማ፣ በስልትና ስትራቴጂ ላይ የሚፈጠር ሆኖ የመተዳደርያ ደንቡና የአደረጃጀት መርሁ በግልፅ ቀርበው መግባባት ከተፈጠረ በኋላ ብቻ ነው መቀጠል የሚቻል፡፡ ብሄር ላይ መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝም እያራመደች ያለች አገር ላይ አንድ ፓርቲ ሲፈጠር በብሄራዊ የክልሎችና የአገር አቀፍ

ፓርቲዎች መካከል ምን ዓይነት ግንኙነት ይኑር? ምን ዓይነት የስልጣንና የስራ ክፍፍል ይኑር? ህብረ ብሄራዊ ፌደራሊዝም የሚከተሉ አገራት ተሞክሮ ምን ይመስላል? በአገራችን እንዴት ይስተናገዳል? የውክልና፣ የአመራር ስርዓት፣ እኩልነትና ነፃነት፣ የጋራ ተጠያቂነት...ወዘተ እንዴት ነው የሚሆነው በሚሉት ጉዳዮች ላይ ሙሉ በሙሉ መግባባት ሳይፈጠር በአዋጅ የሚፈፀም ውህደት ከቶም የለም፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚፈጠሩ ዓበይት ልዩነቶች በራሳቸው ወደ ውህደት የሚወስዱ አይደሉም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ጉዳዮች አንድ ወጥ አገራዊ ውሁድ ፓርቲ ለመፍጠር ዋነኞቹ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡

v/ **አምስተኛ**፡- መሰረታዊው የውህደት ነጥብ በፍፁም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ሂደት ላይ እንዲመሰረት የማድረግ ነጥብ ነው፡፡ የውህደት ዋነኛው ጉዳይ አካላዊ ጥምረት ሳይሆን አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብና አመለካከትን ወደ ላቀ የመግባባትና መተማመን ደረጃ በማሸጋገር ያልነበረ አዲስ አቅምና ብቃት የምትፈጥርበት የተለየ መድረክ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ሂደት ሄዶ ሄዶ ሰፋፊ ክርክሮች፣ ሰፋፊ ውይይቶች፣ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሑፎችና ሃሳቦች፣ የሚቀርቡበት ነው፡፡ ልዩነቶችን ለማጥበብ ተከታታይና ተደጋጋሚ መድረኮች የሚፈጠሩበት ነው፡፡ በዚህ አሰራር ብዙ አዲስ የሰው ሃይል ከላይ እስከ ታች የሚገነባበትና የሚፈጠርበትም ነው፡፡ በአመለካከት ጥራት በአብዮታዊ ስነ-ምግባራቸው የታነፁ የጠነከሩ አባላትና አመራሮች፣ አሰራሩና አደረጃጀቱ የጠራና የሰላ ትግልና የተሟላ ዲሞክራሲያዊ ህይወት የሚረጋገጥበት ሂደት በማድረግ ብቻ ነው ሊፈፀም የሚገባው፡፡ ለዚህ ሲባል በየጊዜው ግልፅ የሆኑ አጀንዳዎች እየቀረፁ፣ ከላይ እስከ ታች ሰፋፊ መድረኮች እየፈጠሩ፣ የስራ አስፈፃሚ፣ የማእከላይ ኮሚቴ፣ መላው ካድሬና አባል፣ ከውህደቱ ተጠቃሚ የሆነው ህዝብ በተለይ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ማህበራዊ መሰረት የሆነው አርሶ አደርና የከተማው ኗሪ... ወዘተ በነፃነት ክርክር ሊያደርግበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ የውይይት መድረኮች፣ ሰሚናሮችና ኮንፈረሶች፣ ስልጠናዎች ከተካሄዱ በኋላ በመጨረሻ በጉባኤዎች የሚፀድቅ እና የሚፈፀም ይሆናል፡፡

እንደዚህ ባለ ሰፊ፣ ጥልቅና የዲሞክራሲያዊ ሂደት ሳያልፍ የሚፈፅም ውህደት አይኖርም፡፡ አንድ መሪ ውህደት እንፈፅማለን ስላለ ብቻ የሚተገበር ውህደት የለም፤ ድርጅትን ሊበተን ካልሆነ በስተቀር፡፡

ለማጠቃለል ያህል የአንድ ውሁድ ፓርቲ ጥያቄ ታድያ ምን ይሁን? የጊዜ ጉዳዩ ወደ ጎን ትተን ሳይሆን እነዚህን መሰረታዊ ሂደቶች ማለፍ የግድ ይላል፡፡

## II. ኢህአዴግን በአቋራጭ አንድ ፓርቲ ለማድረግ የሚፈልገው ኃይል ዓላማና ህልም

### 2.1. የኢህአዴግን መለያዎች የማፍረስ ዓላማና ህልም

#### 2.1.1. ወደ ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ የመሸጋገር ዓላማና ህልም

i) ኢህአዴግን ወደ አንድ ፓርቲ የመለወጥ አመለካከት እያነሳ ያለው ሃይል እንደ መከራከሪያና ሽፋን "ጥናት ተደርጎ ነው፣ በጉባኤ ላይ የተወሰነ ነው፣ እንዲሁም እየተነሳ የቆየ ጉዳይ ነው" የሚሉ ነጥቦች መከራከሪያው እንደሚያደርግ የሚገመት ቢሆንም፣ በዋናነት ግን ኢህአዴግ የተታገለለት በኢትዮጵያ ሁኔታ የሞት ሽረት ጉዳይ የሆነውንና የሚለይበትን ዴሞክራሲ አጥፍቶ ወደ ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ በመሸጋገር ፈላጭና ቆራጭ የመሆን ህልም ነው:: ይህን ህልም የተለያዩና በርከት ያሉ ዋና ዋና መገለጫዎችን ተጠቅሞ ማየት ተገቢ ነው:: አንድ መገለጫው ኢህአዴግ በአንድ ፓርቲ ስም አጥፍቶ ከዚህም ከዛም ሃይሎችን አሰባስቦ በፈላጭ ቆራጭነት በቀጭን ትእዛዝ የሚተዳደርና የሚገዛ ፓርቲ የመመስረት ፍላጎት ነው:: ይህ የተማከለ ንጉሳዊ የሚመስል መንግስታዊ ስልጣን ይዞ ለመቀጠል እንደ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል አንድ ፓርቲ የመፍጠር ህልም ነው:: ከዚህ ጋር በተሳሰረ በቀጣይ ለሚታሰበው ፕሬዚደንሺያል የምርጫ ስርዓትና ይሄን አካሄድ ተጠቅሞ ብዙ ቁጥር ያላቸውን በመያዝ ጥቂቶች በቀጣይነት ተረግጠው የሚሄዱበት የብዙ ቁጥር አገዛዝ የሚፈጥር (totalitarian) አዲስ ፀረ-ዴሞክራሲ ስርዓት እንደ መሳሪያ የሚያገለግል ነው:: ይህን በመጠቀም ኢትዮጵያን በአንድ ብሄር ፍፁማዊ አገዛዝ ስር የማስገባት ህልም ነው::

ii) ኢህአዴግን ወደ አንድ ፓርቲ የመቀየር ሌላው ፀረ-ዴሞክራሲ ዓላማ ደግሞ የህብረ-ብሄርና ክልሎች ስልጣን በአንድ ፓርቲ እና አንድ መሪ ስር እንዲወድቅ በማድረግ አንድ ወጥ የሆነ አሃዳዊነትና አሃዳዊ ስርዓት የመመለስ ህልም ነው:: ሕብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝም ደረጃ በደረጃ እንዳይገነባ ከሚያደርጉ ማነቆዎች ውስጥ አንዱ የተማከለ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስርአት ነው:: ይሄ አካሄድ ማለትም የተማከለ የፖለቲካ ፓርቲ ስርአት ማዕከላዊነትን በማጠናከር ክልሎች ወይም ብሄሮች በራሳቸው ጉዳይ ላይ የሚኖራቸው ወሳኝ ድምፅ (veto-power) በመገደብና ፌዴራል መንግስትንም የመቆጣጠርና የመገደብ አቅማቸውን በማዳከም እውነተኛ ህብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝም ስርዓት እንዳይቀጥል በማድረግ ብሄራዊ ጭቆናን እንደ አዲስ የሚፈጥር ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናቶችን ካካሄዱ የተለያዩ ምሁራን አንዳንዶቹ በጥብቅ ያስቀመጡት፣ ያልተማከለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ስርዓት መኖሩ ህብረ-ብሄራዊ ፌዴራሊዝምን ለመጠበቅ አንደኛውና ትልቁ ቅድመ ሁኔታ ነው:: አንድ ፓርቲ ክልሎችንና ፌዴራልን በአንድ ላይ የሚቆጣጠር ከሆነ ስርዓቱ ያልተማከለ ሳይሆን የተማከለ ነው ማለት ነው:: ይልቁንም በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች የግንባር ፓርቲ አደረጃጀት እየተዳከመ ሳይሆን እየጠነከረ እንደሚሄድ የሚያመላክቱ ፅሑፎች ብዙ ናቸው:: በመሆኑም አሁን ያለው ወደ አንድ ፓርቲ የመቀየር ህልም ማንነት ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝምን ለማጥፋት ያለመ ነው::

iii) አንድ ፓርቲ፣ የዜጋ ፖለቲካና አሃዳዊት ኢትዮጵያን አቀናጅቶ ህብረ-ብሄራዊነትን ማጥፋት፣ አሃዳዊነት ወይም አንዲት ኢትዮጵያ በአዲስ ማደናገሪያ ፈጠራ የማስገባት ፀረ ዲሞክራስያዊ ሂደት ነው፡፡ ወደ አንድ ፓርቲ ሂደት ከተገባ አፈፃፀሙ የተለየ ስምምነትና ማስተካከያ ካልተደረገበት የሁሉንም ብሄራዊ ፓርቲዎች ሕጋዊና ፖለቲካዊ ህልውና የሚያጠፋ ነው፡፡ ከዚያም አልፎ እነዚህ ብሄራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባሎቻቸውን፣ አመራራቸውን፣ ደጋፊዎቻቸውና፣ ተቋሞቻቸውንና ፋይናንሳቸውን …ወዘተ በአንዴ የሚያጡበት ሂደት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ልክ በናይጄሪያና በኬኒያ በማንነት የሚደራጅ ፓርቲ እንዳይኖር በሕግ እንደታገደ ሁሉ ተመሳሳይነት ያለው እርምጃ በመውሰድ የብሄር ብሄረሰቦች ፓርቲዎችን ህልውና ከመሰረቱ ማጥፋት ነው፡፡ ይሄን በማድረግ የተመረጠ አገራዊ ፓርቲ ምድብተኛን የክልል፣ የዞን፣ የወረዳ የፀጥታ ሓይልና መከላከያ ሹመኛ አድርጎ የብሄሮችን ማፈንና ሰጥ ለጥ አድርጎ ረግጦ መግዛት ነው፡፡

iv) አሁን እያደገ ያለው የዜግነት ፖለቲካ ከዚህ ጉዳይ ጋር በጥብቅ የሚተሳሰር ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ በአሃዳዊ ፓርቲ አማካኝነት ብዝሃነትን ማክሰም ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ መሰረቱ የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ሆኖ፣ በግልፅ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ የብሄር ብሄረሰቦች መብት በመግሰስ አሃዳዊ ኢትዮጵያ ለመመለስ አንድ ፓርቲ መመስረት አስፈላጊ መሳሪያ ሆኖ በዘመቻ እየተሰበከ ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ (civic nationalism) ምንም እንኳን በፈታኝ ሁኔታዎች የቡድኖች መብትን የሚቀበል ቢሆንም፣ ዋናው ይዘቱ ግን የዜጎች መብትና እኩልነት ከተረጋገጠ የቡድን መብት አያስፈልግም የሚል ነው፡፡ ከብዙ ማንነት ይልቅ አንድ ማንነት ብቻ እንዲጠነክርና እንዲገነግን የሚሰራ ስለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ይምራ፣ የብሄር ማንነት ይጥፋ፣ የሚለውን ዋና መፈክሩ አድርጎ አንድን ብሄር በተለያዩ ክፍለ አገሮች በታትኖ የሚያጠፋ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኢህአዴግ አንድ ፓርቲ ምስረታን እንደ ማሳለጫ ቁልፍ አጀንዳ በመውሰድ የሚሰራበት ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ በይፋ እያራመደ ያለው ሃይል ደግሞ የተደራጀ የትምክህት ሃይልና የሱ መሳሪያ የሆነው በስልጣን ላይ ያለው ሃይል ውህደት በመፍጠር እንደ አመለካከት እየተፈጠረ ያለው አንድ ፓርቲ መሰረት ተደርጎ እየተሰራ ነው ያለው፡፡

v) የዚህ ሁሉ ድምር አንድ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መገለጫ የሆነውንና ህዝቦች አያሌ መስዋእትነት ከፍለው ያረጋገጡትን ራስን በራስ ማስተዳደርና የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን ቁልፍ ሕገ መንግስታዊ መብት የማጥፋትና የመፋቅ ዓላማ ያለው ነው፡፡ የተቀመጡትን ህልሞች ለማሳካት የሚፈጠረው የተዋሃደ የኢህአዴግ አንድ ፓርቲ፣ ይሄን ተፈጥሮአዊ፣ ብሄራዊና ብሄረሰባዊ መብት አፍኖ የሚይዝ ነው፡፡ አንድ ውሁድ ፓርቲ የማደራጀት ህልም፣ የክልሎችና የፌደራል ጂኦግራፊያዊ ፌደራሊዝም በመፍጠር የሁሉም ስልጣን ብቸኛ ባለቤት በመሆንና የብሄሮች ማንነት ወደ ጂኦግራፊያዊ አስተዳደር በመቀየር የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ከመሰረቱ ለማጥፋት ያለመ ነው፡፡ ሉኣላዊ ስልጣን በብሄር ላይ የተመሰረተ ክልላዊ አስተዳደርን የሚያጠፋ ነው፡፡ በአጠቃላይ፣ አሁን ባገራችን ቁልጭ ብሎ እየታየ ያለው ፀረ ህብረ-ብሄራዊ ማንነት ፖለቲካ፣ በዚህ አጥር ውስጥ ኢህአዴግ ወደ

አንድ ፓርቲ ተሸጋግሮ ምርጫ ካሸነፈ፣ በመጀመሪያ የሚወስደው እርምጃ ህብረ-ብሄራዊ ፌደራሊዝምን ማስወገድና ማፍረስ ነው፡፡ ይሄ በአፍሪካ ታሪክ በተለየ መራራ ትግል በህወሓት/ኢህአዴግ የተገኘውን አገርንና ህዝብን በሰላም የሚያኖር ሞዴልና ታሪካዊ ድል የሚደመስስ ነው፡፡ ይህ መተግበር በሚጀመርበት ወቅት ብዙ ቁልፍ መብቶችን የሚደነግገው የሕገ መንግስት አንቀፆችን እንዳለ የሚያፈርስ፣ ያለ ምንም ጥርጥር አገርን የሚበትን ይሆናል፡፡

vi) አንድ ፓርቲ ፈጥሮ ፈላጭና ቆራጭ የመሆን ዓላማና ህልምን ለማሳካት በታቀደና በተደራጀ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ያለው ሃይል መሰረታዊ ባህሪው ፀረ-ዴሞክራሲ ስለሆነ ከላይ በተገለፁት የዴሞክራሲ ጥሰቶች ብቻ የሚመለስ አይደለም፡፡ ሁሉንም ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚያግድ ነው፡፡ የመደራጀት፣ በተደራጀ መንገድ የመቃወም፣ የመናገር ነፃነት... ወዘተ ትልቅ መንግስታዊ ር ይዞ ሊያምበረክክ ጥረት ያደርጋል፡፡ የስልጣን ሃይሎች ሚዛናዊነትም ይዛባል፡፡ ፈፃሚው አካል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን፣ ፍርድ ቤቶችን፣ የህግ ተርጓሚዎችንና እንዲሁም የሚድያ ተቋማትን በበላይነት ተቆጣጥሮ እንዲይዝ የሚያደርግ ነው፡፡ በመሆኑም የሕግ የበላይነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚባል ነገር ሊጠፋ ነው ማለት ነው፡፡ (ልክ አሁን እየታየ እንዳለው) በእንደዚህ አይነት ኢ-ፍትሃዊ አስተዳደር የሚገለፀው የፖለቲካ ችግር ብቻ ሳይሆን፣ የሃብት ክፍፍልም ይዘቱን እየሳተ ስለሚሄድ፣ የዜግነት ፖለቲካ በራሱ በሰው ልጆች ላይ ልዩነት የሚያደርግ ስለሆነ፣ ይህ ሁሉ ተደምሮ በጥገኛ መበስበስ ሂደት የሚመሰረት አንድ ፓርቲና መንግስት በመሆን በፀረ-ዴሞክራሲና ፀረ-አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባህሪው ተጠናክሮ የሚወጣ ነው፡፡

### 2.1.2. አብዮታዊ ዴሞክራሲንና መሪ ፓርቲውን የማጥፋት ዓላማና ህልም!

i) በአቋራጭ አንድ ፓርቲ መስርቶ ጥገኛ ስልጣኑን ሊያራዝም የሚረባረበው ሃይል ሌላ መሰረታዊ ዓላማው አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርናን መሪ ፓርቲውን (የነባሩ ኢህአዴግ መለያ) በአንድ ፓርቲ ምስረታ ሂደት ለመቅበር ያለመ ነው፡፡ በተለያዩ የዚህ ፅሑፍ ክፍሎች እንደተገለፀው፣ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ጊዜው ያለፈበትና እንደማይሆን በመደምደም በሊበራል ዴሞክራሲ ሽፋን በይዘቱ ኪራይ ሰብሳቢ የሆነ አንድ ፓርቲ የመፍጠር ህልም ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ቁልፍ ጉዳይ ኢህአዴግ ምትክ የሌለው አገራዊ ሸክም ይዞ ተልእኮውን የሚያስፈፅም ጠንካራ የራሱ መለያ ስነ-ሃሳብ ይዞ ስነ-ሃሳቡንና የኢኮኖሚ ሞዴል መመሪያ ጨብጦ፤ አመራር፣ አባላትና ካድሬዎች በተነፃፃሪ ብቃት ፈጥሮ ህዝብ ድረስም ገብቶ እንደ ጠንካራ መሪ ፓርቲ ሲንቀሳቀስ የነበረ መንግስትን የሚመራ ድርጅት የነበረ ሲሆን አሁን አንድ ፓርቲ ለመፍጠር በሚል ሽፋን ደካማ፣ ፋይዳ የሌለው ፓርቲ፣ የመንግስት ቢሮክራሲያዊ አወቃቀርን በማጠናከርና በማፈርጠም ፓርቲ ኖረ አልኖረ ለውጥ የማያመጣ የይስሙላ ፓርቲ እንዲሆን በማድረግ ህዝብን

ለማደናገር ስም፣ አርማ፣ ቅርፅ በጠቅላላ ደግሞ ይዘቱን ቀይሮ አሻንጉሊት የሆነ ፓርቲ መፍጠር፣ በሊበራል ፓርቲ ሽፋን ጥገኛ ፓርቲ ማጠናከር ፖለቲካዊና ሕጋዊ ጉዳዮችን ተጠቅሞ ኢህአዴግን መቅበር ነው፡፡

ii) አብዮታዊ ዴሞክራሲንና መሪ ፓርቲውን አጥፍቶ የሚፈጠር አንድ ሰው ወይም ቡድን እንደፈለገ የሚያደርገው አንድ ፓርቲ የዓላማና አገራዊ ተልዕኮ ያለው መሪ ፓርቲ ሳይሆን የምርጫ፣ የወንበር ፓርቲ፣ ይሄም በጥረት እየተቧደነ ለስልጣን ብቻ የሚጠቀምበት ፓርቲ መመስረት ነው፡፡ ስለዚህ አገርን የሚመራ ፓርቲ ሳይሆን፣ በየአምስት ዓመቱ በሚደረግ ምርጫ የሚሰባሰብ፣ ምርጫ ካለፈ በኋላ እርስ በርሱ የሚጠፋፋና የሚባላ ፓርቲ ነው የሚሆነው፡፡ ልክ በብዙ የአፍሪካ አገሮች እንደሚታዩ የምርጫ ፓርቲዎች፣ ምርጫ ሲመጣ እንደሚታዩ የመስቀል ወፍ ፓርቲዎች ተመሳሳይ ፓርቲ መፍጠር ነው፡፡ መሪ (ቫንጋርድ) ፓርቲን በማጥፋት የሆይ ሆይ ፓርቲ መፍጠር ነው፡፡ ይህ ሲባል፣ ዓላማና ራዕይ የሌለው ስልጣንን መሰረት አድርጎ የሚደራጅ ፓርቲ ነው መነሻውና መድረሻው፡፡

iii) ሌላው ዓላማውና ህልሙ ህወሓትንና የትግራን ህዝብ መምታትና መነጠል ነው፡፡ ህወሓትና የትግራይ ህዝብ በታሪክ አጋጣሚ ለዚህ የአገርና የህዝብ ዋስትና የሆነው መስመር ቀድመው ባለቤት በመሆን በኢህአዴግ ውስጥ የሚያካሂዱትን ትግልና ለመስመሩ ያላቸውን ተገዢነትና ተአማኒነት በሌላ ሊሸረሽሩት ስላልቻሉ፣ ህወሓት ካልጠፋ ደግሞ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ህልውና ስለሚቀጥል፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ማጥፋት ህወሓትን ከማጥፋትና የትግራይን ህዝብ ከማዳከም ውጭ ፋይዳ እንደሌለው በመደምደም ታሪካዊ የኢህአዴግ ባለቤት የሆነው ህወሓት ተገዶ ከግንባሩ እንዲወጣ በማድረግ፣ ተነጥሎ እንዲመታ፣ እንዲመክንና ሌጋሲው እንዲጠፋ መሰረት ያደረገ ዓላማ አለው፡፡ የሌለውን ወይም የተዳከመውን ህወሓት ተጠቅመው የትግራይ ህዝብ ያስመዘገባቸውን ድሎች ማደብዘዝ፣ ትግራይን በቁጥጥር ስር ማዋል፣ የሞግዚት መንግስት መመስረት ....ወዘተ የመሳሰሉ ህልም ያለው ነው፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ልማታዊ ዴሞክራሲ፣ ክልል፣ ብሄር ብሄረሰብ፣ ለሚባሉ ፖለቲካዊ ስነ-ሓሳቦች ባለው የቀረና ጥላቻ የኤርትራው ፕሬዚዳንት ኢሳያስ "እነዚህን ከታሪክ ለማጥፋት የፖለቲካ እጥበት ማካሄድ" እንዳለው አሁንም ] ፓርቲ መፍጠር በሚል ሽፋን ህወሓትን መፈናፈኛ በማሳጣት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዕጥበት ለማካየድ ያለመ ነው፡፡ ህወሓትን ለማገድ፣ ለመወንጀል፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ መሰረት ለማሳጣት፣ ኢኮኖሚያዊ ዓቅሙንና ማሕበራዊ መሰረቱን በከፍተኛ ደረጃ ለማዳከም አንድ ፓርቲ መመስረት እንደ ቁልፍ መሳሪያ ተወስዷል፡፡

**2.2. በፀረ-ዴሞክራሲ መንገድ የመዋሃድ ዓላማ!**

i) በዚህ ውስጥ ፅሑፍ ተደጋግሞ እንደተገለፀው፣ መዋሃድ ያስፈልጋል፣ አያስፈልግም የሚለው ሌላ ጉዳይ ሆኖ፣ የመዋሃዱ ሂደት ግን በፍፁም ዴሞክራሲያዊ አካሄድ ሊፈፀም እንደሚገባ ከዚህ ውጭ የሚፈፀም የመዋሃድ ሂደት ግን ፀረ-ዴሞክራሲ ከመሆኑም አልፎ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ሊፈጥር እንደማይችል

ተቀምጧል፡፡ ይሁን እንጂ የኢህአዴግ የመዋሃድ ጉዳይ በይፋ በአደባባይ ላይ በፍፁም ፈላጭ ቆራጭነት ታውጇል፡፡ ስራ አስፈፃሚም ሆነ የኢህአዴግ ምክር ቤት ያስቀመጠው አቅጣጫ ተጠንቶ ሃሳብ ወይም ጥናት እንዲቀርብለትና አንድ ፓርቲ እንሁን ወይስ እንዳለነው እንቀጥል ወይም ደግሞ ምን ሌላ አማራጭ አለ ብሎ በጥልቀት ተወያይቶ፣ ተከራክሮ አቅጣጫዎች እንዲያስቀምጥ የተወሰነው የድርጅት ውሳኔ ተቀይሮ በፍፁም ማን አለብኝነት ከፓርቲው ጠንካራ አሰራርና ዲስፐሊን ውጭ ኢህአዴግ በቅርብ ጊዜ አንድ ፓርቲ እንደሚሆን ይፋ ተደርጓል፡፡ ግለሰብ መሪ ራሱን ከድርጅት በላይ አስቀምጦ ልክ እንደ አመጣጡ በኔት ዎርክና ውስጥ ለውስጥ በሚደረግ ሴራ ጉዳዩ እንዳለቀለት ተወስዶ "ቅር ያለው ገደል ይግባ" የሚል ዓይነት አምባገነን ጫፍ ላይ ደርሶ ይገኛል፡፡

ii) በዚህ ጉዳይ ላይ የተደረገ ጥናት በአግባቡ ቀርቦ የተደረገ ውይይት፣ ክርክር፣ ልዩነቶችና የሚያስማሙ ጉዳዮች አስመልክቶ የተጀመረ ምንም ነገር የለም፡፡ ድሮም ለስሙ እንጂ በዴሞክራሲያዊ አሰራር ለመፈፀም ታስቦ አልነበረም፡፡ ቢሆንም ግን በዚህ ደረጃ ለይስሙላም ቢሆን ጥናቱ ቀርቦ ለሽፋን የሚሆን እንኳን ትንሽ ንግግርም በሌለበት ሁኔታ በፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ ኢህአዴግን የማፍረስ ስራው ከሞላ ጎደል ተፈፅሞ ይገኛል፡፡ ስርዓቱና መንገዱ ሰፋፊ ውይይቶችና ክርክሮች፣ በፓርቲ ውስጥ፣ በሕብረተሰብ ደረጃ በተለይ ደግሞ በማሕበራዊ መሰረታችንና ለዚህ የሚሆኑ ሰፋፊ፣ ተከታታይና ብቁ ጊዜ የተሰጣቸው የኮንፈረንስ መድረኮች፣ ሰሚናሮች፣ ስልጠናዎች ..... ወዘተ ተዘጋጅተው፣ ብቁ ጅንዳዎች ተቀርፀው ሊፈፀም ይገባው ነበር፡፡ የዚህ ሽታና ምልክት የለም፡፡ ያለ ምንም ሃፍረት ከኢህአዴግ ጉባኤ በላይ በመሆን ባለማወላወል ድርጅት ወደ ማፍረስ የተደረሰበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡ ከዚህ የሚከፋና ከዚህ በላይ የፀረ-ዴሞክራሲ መገለጫ ሊኖር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ዋናው ይዘቱ ፣ ዓላማውና ህልሙ ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ፣ የአፈፃፀም ሂደቱም ፍፁም ፀረ-ዴሞክራሲ በመሆን ኢህአዴግን የማፍረስ ሂደቱ እየተጠናቀቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.3. የአንድ ውሁድ ፓርቲ ዕጣ አንድነት ወይስ መበታተን?

i) ስም ብቻ ይዞ እስካሁን ዳዴ እያለ የመጣው ኢህአዴግ "አንድ ፓርቲ ማድረግ" በሚል ሽፋን በደ እየተወገደ፣ እየተቀበረ ነው፡፡ በዚህ ፅሑፍ ላይ በተዘረዘሩት የአንድ ፓርቲ ምስረታ የቅድመ ሁኔታ መሰረታዊ ነጥቦችን አሁን በመሪነት ላይ ያለው ፀረ-ዴሞክራሲ ሃይል ተቀብሎ ውህደቱን በዚህ የመፈፀም፣ በህብረ-ብሄራዊነትና በፌደራል ስርዓታችን ላይ በተጨባጭ ሊኖሩ የሚገባቸውን አማራጮች ተከራክሮ ልዩነቱን በማጥበብ የሚያቀራርብ የመፍትሔ ዕድል የማስተናገድ ጉዳይ ስትራቴጂካሊ የተዘጋ ነው፡፡ በስልትም ቢሆን ዝግ ነው ባይባልም እንኳን፣ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ አንደኛው ነገር ድርጅቱ ከገባበት አደገኛ የጥገኛ የመበስበስ ተሃድሶ አድርጎ የመመለስ ዕድሉ ከሞላ ጎደል የሞተ ነው፡፡ ወደ ጥልቅ ተሃድሶ

ገብቶ ራሱን እስካልቀየረ ድረስ ያለው አማራጭ “አንድ ፓርቲ፣ የዜጋ ፖለቲካ አሃዳዊ ኢትዮጵያዊነት” ናቸው መፈክሮቹ፡፡

ii) ይህ ሃይል ኢህአዴግን ቀብሮ፣ እነዚህን መፈክሮች ደግሞ ለጊዜው ሊያደናግርባቸው ካልሆነ በቀር በህብረ ብሄራዊት አገረ ኢትዮጵያ ቁንፁል የዜግነት ፖለቲካና የህብረ ብሄራዊ ማንነት ፖለቲካ የማይታረቁ የፖለቲካ አሰላለፎች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የግልና የቡድን መብቶች በፍፁም የማይነጣጠሉና አንደኛውን ከሌላኛው ዝቅ ወይም ከፍ በማድረግ ወደፊት መራመድ አይቻልም፡፡ ሕገ መንግስታችንም በማያሻማ ሁኔታ ሁለቱንም ጉዳይ አስቀምጦታል፡፡ ሁለቱንም አስተሳስረህ ከመተግበር ውጭ አማራጭ የለም፡፡ በመሆኑም ኢህአዴግ በስመ አንድ ፓርቲ በዜግነት ፖለቲካ መፈክር ላይ የተመሰረተ ፓርቲ ሲሆን የፀረ-ዴሞክራሲ ቁልፍ መሳሪያ ስለሚሆን ከዋናው መሰረቱና መራጭ ህዝብ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች እየተነጠለ ስለሚሄድ በኢትዮጵያ በምርጫ አሸናፊ እየሆነ አይሄድም፡፡ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ህብረ ብሄራዊነትን የሚገልፅ አስተዳደርና ማንነታቸውን የሚያንፀባርቁ የራሳቸው ፓርቲዎች መስርተው መተዳደር ስለጀመሩ አንድ ጨፍላቂ ፓርቲን ዝም ብለው አይቀበሉም፡፡ ቁንፁል የዜግነት ውሁድ አገራዊ ፓርቲ የብሄርና ብሄረሰቦችን ህልውናና መብት የሚያጠፋ ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ ደግሞ 70 እና 80 ብሄሮች እና ብሄረሰቦች ያሏት አገር ስለሆነች፣ ይሄንን መካድ በነባራዊ ሁኔታው አያስኬድም፡፡ በመሆኑም ዕጣው መበተን ነው የሚሆነው፡፡

iii) የዜግነት ፖለቲካና በርሱ ላይ የተመሰረተ ፓርቲ፣ ተግባሩና አስተሳሰቡ ያ የተቀበረው አሮጌው የአገዛዝ ባህሪ ከፍተኛ መሳሪያና ሽፋን ፖለቲካ ስርዓት መሆን ነው፡፡ ይህ ማለት በትግልና አያሌ መስዋእትነት የተገኘውን የብሄርና የብሄረሰቦች መብት በመፃረር ተመልሶ ወደ ብሄርና ብሄረሰቦች ጭቆና የሚያስገባ ነው፡፡ አሁንም የትምክህተኛው እንቅስቃሴ በይፋ እየሄደበት ያለ ነው፡፡ ይህ አፈና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የሚለውን ጭራሽ የሚቃወምና ተግባር ላይ የማያውል ነው፡፡ ካሁን በኋላ ዳግም የብሄር የበላይነትን ቀንበር የሚሸከም የለም፡፡ በዚህ አጠቃላይ ሂደት ደግሞ በእኩልነት ላይ በተመሰረተ አንድነት የመኖር ዕድል እየጠበበ ተስፋ መቁረጥን ስለሚያስከትል፣ የመገንጠል መብት፣ የነፃ መንግስት ፍላጎት እና አመለካከት እየጎለበተ ይሄዳል፡፡ አሁንም እየታየ ያለው ምልክት ነው፡፡ ይህ በሃይል ደም በመፋሰስ፣ ወይም በሰላም የማይቀር የብተና ሂደት ሆኖ ይመጣል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም፣ ውጤቱ መበተን ነው፡፡

iv) በኢትዮጵያ ታሪክ ራሱን ሊደግም ይችላል፡፡ በሚካኤል ጎርባቾቭ ጊዜ 74 ዓመታት ያስቆጠረው የሶቭየት ህብረት ካምፕ መፈራረስና የዩጎዝላቪያ መበታተን በአገራችንም ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ያን ጊዜ የነበረው ስልጣን፣ አመራርና የሶቭየት ሕብረት መበታተንና አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አካሄድ በብዙ መልኩ የሚመሳሰል ነው፡፡ በሚካኤል ጎርባቾቭ ጊዜ የፈራረሰችው ሶቭየት ህብረት ብዙ የሚተሳሰሩ ምክንያቶች

የነበሯት ቢሆንም፣ የወደቀው የጎርባቾቭ አመራር ግን ለሁነቱ በዋናነት የሚነሳ ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ የፓርቲ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሪፎርም በሚል ስም የተካሄዱ አውዳሚ ተግባሮች እንደሆኑ ይገለፃል፡፡ ጎርባቾቭ ሁለት የሚተሳሰሩ የፖሊሲ ሪፎርሞች አስተዋውቆ ነበር፡፡ “ግላስኖስት” ማለትም አዲስ ሙብት፣ የመናገር ነፃነት፣ የሚድያ ነፃነት… ወዘተ የሚል ይዘት ያለው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ “ፒሪስትሮይካ” ማለትም አዲስ የኢኮኖሚ ማስተካከያ ነበሩ፡፡

v) የሁለቱም ሪፎርሞች ይዘት ጎርባቾቭ የራሱን ቡድን ወደ ስልጣን በማምጣትና የሚቃወሙትን ጠራርጎ በማስወገድ ጀምሮ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ፓርቲውን ጠቅልሎ ወደ ማዳከም ሄደ፣ የነበረውን ነባሩን ፖሊት ቢሮ አስወገደ፣ በይፋ የሚድያ ነፃነት ብሎ አወጀ፣ በዚህም የፓርቲውን የሆነውንም ያልሆነውንም ድክመት አጋለጠ፣ ሁሉም ዜጋ ያለ ምህረት እንዲነቅፈው አደረገ፣ ካድሬዎችም በፓርቲው ላይ እንዲነሱ አደረገ፣ የኮሚዩኒስት ፓርቲ ስብሰባዎችና ጉባኤዎች በቀጥታ የቴሌቭዥን ስርጭት እንዲተላለፉ አደረገ፣ ቁልፍና ጠንካራው ነባር አመራሮች እንዲጠሉና እንዲገለሉ አደረገ፣ ብዙዎችን በጡረታ አሰናበተ፣ ጎርቫቾቭ ወደ ፓርቲው ሊቀመንበርነት እንደመጣ ፓርቲውን እንደተወው በግልፅ አላወጀም፣ አልፎ አልፎ ለይስሙላ ሶሻሊስታዊ ሪፍርም ነው እያካሄድኩ ያለሁት ይል ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ግልፅ የሆነ ሮድማፕ ሊገልፅ አይፈልግም ነበር፡፡ በኢኮኖሚ ዙሪያም የነበረውን የኢኮኖሚ ፖሊሲንና ስትራቴጂን በግልፅ በመቃወም፣ በብዙ ጉዳዮች ላይ ምዕራባውያን እንዲገቡ አደረገ፡፡

vi) በስተመጨረሻ ደግሞ ሁለት እርምጃዎችን ወሰደ፡፡ አንደኛው፣ የሶቬትዩኒየን ኮምዩኒስት ፓርቲን በሕግ አፈረሰው፡፡ ሁለተኛው፣ ራሱ ጎርባቾቭ በቀጥታ የአገር ፕሬዚደንት ሆኖ መመረጥ በሚያስችለው ሁኔታ ሕገ-መንግስቱን አሻሻለው፡፡ በሂደት ዋናው መሪ ፓርቲ እየሞተ አዳዲስ ብሄራዊ ሃይሎች እንዲያይሉ አደረገ፡፡ እስረኞችንም ፈታ፣ ፓርቲውን ለመድፈርና ለማሸነፍ፣ ምርጫ ጠርቶ በውጤቱም የኮምዩኒስት ፓርቲ ዕጩዎች ተሸንፈው ሊበራል ሪፎርሚስት የሚባሉ አሸነፉ፡፡ ብሄራዊያን ሃይሎች በማየላቸው ሶቬየት ህብረትን እየጠሉ በመምጣታቸው የምዕራቡ ዓለም ሴራ ተጨምሮበት የመገንጠል አመለካከቶች እየጠነከሩ ሄዱ፣ ጎርቫቾቭ ባሻሻለው ሕገ-መንግስት መሰረት በቀጥታ ተመርጦ ስልጣን ያዘ፡፡ ከዛ በኋላ በሶቬት ህብረት የነበሩ አገሮች ነፃ አገር ለመሆን ስላወጁ፣ 74 ዓመታት የቆየውን ህብረት አፍርሶ ስልጣኑን ለቀቀ፡፡ በግላስኖስት ሪፎርም ስም ፓርቲው ሙሉ በሙሉ ተዳክሞ መበታተንን አስከተለ፡፡ ያን ሁሉ ሲያደርግ ጎርቫቾቭን የሚታገለው አልነበረም፡፡ ትልቅ አደርባይነትና ሽሽት ነው የነበረው፡፡

በዩጎዝላቪያም በሰርቪያ የበላይነት ላይ የተመሰረተ የፌደራል ስርዓት ሊገነቡ ይፈልጉ የነበሩ የተለያዩ መሪዎች በፈጠሩት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ችግሮች ከባድ የአገራዊ ግንባታ ጉድለትና በተለይ ክሮሺያና ስሎቫኒያ የሰርቪያን ብሄርተኝነት በመቃወም ራሳቸውን እንደ ነፃ አገር አውጀው ለተቀሩት

ክልሎችም የመገንጠል ፍላጎትን አደፋፍረውና ነፃነታቸው አውጀው በከባድ ደም መፋሰስ ዩጎዝላቪያ ተበተነች፡፡

### iii) በፓርቲ ውህደት ጉዳይ ላይ የህወሓት ቱባ አቋምና ዋነኛ የመታገያ አቅጣጫዎች

i) አሁን በአገራችን ያጋጠመው ውስብስብ ፖለቲካ አንድ ውሁድ ፓርቲን በሚመለከት በኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ ቁልፍ ነጥበ መቀይሮ (turning point) ሊወሰድ ይገባል፡፡ በመሆኑ ተኛ ጥንቃቄ፣ ጥበብና ቆራጥነት ሊመራ ይገባል፡፡ አቅም የፈቀደውን ያህል የመታገያ መነሻ ፅሑፍ ለማዘጋጀት ያነሳሳውም የነጥበ መቀይሮነቱ ሚዛን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሶስትና አራት በጣም የተቆራኙ አንደኛው ከሌላኛው በኋላ ሳይሆን ጎን ለጎን የሚፈፀሙ የመመከቻ ነጥቦችን ለይቶ ወደ ትግል መግባት ሊያስፈልግ ነው፡፡ እየተቀበረ ያለውን ኢህአዴግ አልቅሰን እንሸኘው ወይስ ሙሉና የተጨበጠ አማራጫችንን ይዘን ቀርበን ትግላችንን እናጋግል፣ ሁኔታው የፈቀደልንን ያህል እንሂድ፣ በሚለው ሃሳብ ላይ ያለጥርጥር ብቸኛ አማራጫችን አሁንም ይሄ ሊሆን ነው፡፡

ii) በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የመመከቻ አቅጣጫችን ካሁን በፊት ካስቀመጥነው አቅጣጫ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ባለፉት ፅሑፎቻችንና ውሳኔዎቻችን ኢህአዴግን እንደ አንድ መታገያ መድረክ ወስደን እንታገልበት ብለናል፡፡ በዚህ መሰረት በአሁኑ ሰዓት በተነሳው ወሳኝ ጉዳይ ማለትም አንድ ውሁድ ፓርቲን በሚመለከትም እስከ ሄደበት ድረስ ሁለትና ሶስት የሚሆኑ መታገያ አቅጣጫዎች ይዘን እንደ መድረክ እንጠቀምበት፡፡ በዚህ መሰረት አንዱ የኢህአዴግ ችግር በዋናነት የአደረጃጀት ችግር ሳይሆን የአስተሳሰብ ነው፣ በመሆኑም ይሄንን ማእከል ያደረገ ትግልና ማስተካከያ ይኑረን፣ የአስተሳሰብ ሪፎርምን ዋናው ጉዳይ እናድርግ በሚል መስራት፡፡ አንድ ውሁድ ፓርቲን በሚመለከት ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ውህደት የራሱ ሳይንስ፣ መርህና አካሄድ እንዳለው (እዚህ ፅሑፍ ላይ በተዘረዘረው መሰረት) እነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ሳይፈፀሙ የሚመሰረት አንድ ውሁድ ፓርቲ የትም እንደማይደርስ፣ ስለዚህም ወደ ዚህ አሰራር መግባትና መጀመር እንደሚያስፈልግ፣ ህወሓት ደግሞ ለዚህ ዝግጁ መሆኑን ማሳየት፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የያዝነውን አቋም ለመላ አባሎች፣ አመራርና የኢህአዴግ ካድሬ፣ ለመላ የህወሓት አባሎችና አመራሮች፣ ለመላ የኢትዮጵያ ህዝቦች በተለይ ደግሞ ለመላ የትግራይ ህዝብ እንዲሁም ለዓለም ለማሳወቅ በፅሑፎች ላይ የተመሰረተ ውይይት፣ ክርክር፣ በሚድያ በሁሉም ቋንቋዎች ይፋዊ የሆነ ትግል ማካሄድ፡፡ ሶስተኛ፤ ይሄ በኢህአዴግ ውስጥ እየቀጠለ አጋር ድርጅቶች የየብሄራቸውና ብሄረሰባቸውን ፓርቲ ይዘው ድምፅ እንዲኖራቸው የሚያስችል መጠነኛ የሕገ ደንብ ማስተካከያ አድርገን ይግቡ ብለን ለማንነት ፖለቲካ በዋናነት ደግሞ ራስን በራስ ለመወሰን መብት የሚታገሉ፣ የዜግነት ፖለቲካን የሚቃወሙ ሃይሎች መሰባሰቢያ ስለዚህም ደግሞ የብሄርና የብሄረሰቦች የበላይነት ያለው ግምባር የምናደርግበት እድል የሚያሰፋ አቅጣጫ ይዘን እንታገል፡፡

iii) ሁለተኛው እና ከዚህ ከላይ ከተገለጠው መታገያ አቅጣጫችን ጎን ለጎን በጥብቅ መስራት ያለብንና አሁንም ባለፈውም የወሰንነውንና ስራውም የተጀማመረውን፣ ፌደራሊስት እና ሕገ መንግስቱን የሚቀበሉ ሃይሎችን ጉዳይ ማጠናከር ነው፡፡ "ኢህአዴግን ወደ አንድ ውሁድ ፓርቲ ልቀይረው ነው" እያለ ያለው ሃይል፣ ከላይ የተገለፀውን የመታገያ አቅጣጫ ይዘን ብንዋጋም የተወሰነ ጊዜ ቢሰጠን ነው እንጂ የያዘውን መደብ ይተገብራል፡፡ ያ በሚሆንበት ጊዜ እኛ ወደ ውሁዱ ፓርቲ ልንገባ አንችልም፡፡ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ለህዝቦች በተለይ ደግሞ ለትግራይ ህዝብ ትግል ትልቅ ክህደት ስለሚሆን፡፡ ኢህአዴግ ሲቀበር የራሳችንን የተሟላ አማራጭ ይዘን ከውህደቱ ራሳችንን አግልለን ነው የምንቀጥለው፡፡ በዚህ ወቅት ቶሎ ግንባር ፈጥረን አማራጭ ፓርቲ ይዘን ልንቆይ ይገባናል፡፡ እነዚህ ሃይሎች ደግሞ ሕገ-መንግስቱን የሚቀበሉ ፌደራሊስት ሃይሎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- እንደ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ሕገ- መንግስታዊ ግንባር" ወይም "የኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ ፌደራል ግንባር" ዓይነት፣ በዚህ መሰረት ቶሎ ብለን ሁኔታው ሳያመልጥ ለመደገፍ የሚያስችል እርምጃ የምንወስድበት አቅጣጫ ይሄ ይሆናል፡፡ ራስህን አግልለህ መቆየት ምናልባት የበለጠ የሚሆንበት ሁኔታ ካለ እየተከታተልክ የሚታይ ነው የሚሆነው፡፡ በዚህ መሰረት የተጀመረውን ይሄን ለማድረግ የሚያስችለንን ስራ በበለጠ ማፋጠን አስፈላጊ ነው፡፡

iv) ሶስተኛው እና መሰረታዊው ጉዳይ ደግሞ በአንድ ውሁድ ፓርቲ ላይ የሚኖረንን አቋምና ስትራቴጂካዊ ትግል የሚመለከት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሁለት የተቆራኙ መሰረታዊ ጉዳዮች በዚህ ጉዳይ ላይ ሊኖረን የሚችለውን አቋም ይወስናሉ፡፡ አንደኛው፤ ኢትዮጵያ ህብረ ብሄራዊ አገር ናት፡፡ የብሄሮች እና ብሄረሰቦች አገር ናት፡፡ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እስከሚፈጠር፤ ብሄራዊ ትስስሩ ጠቦት ከፍ ያለ ቁርኝት በሂደት እስኪ ፈጠር የመጀመሪያ ቅራኔ ባይሆንም በፓርቲዎች አሰላለፍ ላይ ቁልፍ መመዘኛ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በመሆኑም ብሄራዊ አደረጃጀትን የሚያጠፋ የአገር አቀፍ ውሁድ ፓርቲ አደረጃጀት እስከ መካከለኛው ዘመን ድረስ ተቀባይነት የለውም፡፡

v) ሁለተኛው ቁልፍ መመዘኛ ተጨባጭ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡ጀማሪ ካፒታሊዝም እስከ የነፃ ገበያ ዋና ተዋናዮች መሰረታዊ መደቦች ቡርዡዋና ላባደሩ ቦታቸውን ይዘው የዘመነ ግሎባይዜሽን ትስስር እየተጠናከረ ሁለቱም መደቦች ተጠናክረው እስከ ሚወጡ ድረስ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ኢንዳስትሪ የሚመራው ኢኮኖሚ ሆኖ የኢኮኖሚው እድገት ደረጃ በትንሹ የመጀመሪያው ከፍተኛና መካከለኛ የገቢ ደረጃ እስኪደርስ ያለው ፖለቲካ አንድ ነው፡፡ኪራይ ሰብሳቢ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይ የሆነበት ወይም ደግሞ ያልተሸነፈበት ደረጃ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ በአንድ መልኩ ሰፊ የጥገኛ ኪራይ ሰብሳቢዎች መረብ (ኔት ዎርክ)ያን ብሄር ከለላ አድርገው ትምክህትና ጠባብነት ስለሚስፋፉ ጥገኛ የመበስበስ ዋና ፖለቲካዊ መገለጫ ሆነው ስለሚቀጥሉና ዋና የትግል አቅጣጫው ደግሞ በየብሄሩ የተደራጀ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሃይል መመከት ስላለበት ነው፡፡

vi) በሌላ በኩል ደግሞ በጀማሪ ካፒታሊዝም ብሄራዊነት (Nationalizm) እያበበ ነው የሚወ‹ አድማስ ጠቦት ሌላ የኢኮኖሚ ትሰስር የሚፈልግበት ደረጃ ያልደረሰ በመሆኑ ብሄራዊ መነሳሳት ትልቅ ቦታ ያለው ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት በዚህ ደረጃም የፓርቲዎች ብሄራዊ አደረጃጀት ህልውና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በኢትየጵያ እየተባለ እስካለው ጊዜ ድረስ ብሄርን መሰረት ካደረገ አገራዊ ጥምረት፣ ግንባር ወይም ህብረት ውጭ ውሁድ የሚባል ፓርቲ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም በዚህ አገር እስካለን ድረስ ኢህአዴግ እየተቀበረ ስለሆነ ቶሎ ብለን በብሄራዊ ድርጅቶች ላይ መሰረት ያደረገ አገራዊ መድረክ፣ ግንባር ወይም ጥምረት … ወዘተ ለመፍጠር መታገል ይኖርብናል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ውጭ በኢህአዴግ ስም የሚደረግ የአንድ አገር አቀፍ ውሁድ ፓርቲ ምስረታን ሙሉ በሙሉ ተቃውመን መቆም እና ለህብረ ብሄራዊ ፌደራሊዝም ስኬት መዋጋት ብቻ ነው ያለብን፡፡

vii) ህዝባዊና አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ የሆነውን ይህን አቋም ይዘን ፊት ለፊት ስንገጥማቸው ወይ ደግሞ ይሄ የመፍትሄ ሃሳብ ሳይሳካ ቀርቶ የአገር መበተን ካስከተለ ባለፉት ፅሑፎቻችንም የለየናቸው ከባድ ጫና፣ ፖለቲካዊ፣ ሕጋዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ከዚያም ከፍ ብሎ የፀጥታ አደጋዎችም ከሁሉም አቅጣጫዎች ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በተለይ የመጨረሻው ፍቺ ይህንን ጉዳይ ሊያፋጥነው ይችላል፡፡ አይሆንም ላለሁሉም "እምቢተኛ ነው፣ አገር በታኝ ነው"… ከሚል ጀምሮ እስከ ማገድ የሚሄድና ሌሎች አደጋዎችም ሊመጡ ይችላሉ፡፡ ይህ አደጋ ብቻ ግን አይሆንም፤ የትግል ዕድሎችም ይፈጠራሉ፡፡ በህዝባችንና በድርጅታችን ጉልህ መጠናከር በኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የተሻለ ተነፃፃሪ መነሳሳት እንዲሁም በሕገ-መንግስትና ፌደራሊስት ሃይሎች … ወዘተ ዘንድ ልፍ ለይቶ ትግልና መተናነቅ የሚፈጠርበት ሂደትም ይሆናል፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን ፈተናዎችንና አደጋዎችን ለመከላከል ዕድሎችን መጠቀምና ማስፋት አሁንም በጥንካሬያችን፣ በመርህ ላይ በተመሰረተ አንድነታችንና ፅናታችን ላይ ብቻ የሚንጠለጠል ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ዕድገቶች ግምት ውስጥ በማስገባት አጠቃላይ የፖለቲካዊ፣ የፀጥታና ኢኮኖሚያዊ ዝግጅቶቻችንን በተለይ ደግሞ በንቃት የሚቆም ወጣት ከመፍጠር ጎን ለጎን የፀጥታ ዝግጅታችንን መልሶ በጥልቀትና በዝርዝር መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

**አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ህያው ነው! እናሸንፋለን!!**

**መጋቢት 2011 ዓ.ም**

**መቐለ**